Dmujids Volume 6 Issue II 2022 DOI: 10.20372/dmujids 1000

# የብሄር ጥያቄ፣ ብሄርተኞች እና የአማራ ህዝብ ከ1960ዎቹ ጀምሮ

*Derb Tefera[1]*, Genanew Jenberu[2], Adane Mengist[2]*

[1]Department of History and Heritage Managmnet, College of Sciel Sciences and Humanities, Debre Markos University, Debre Markos, Ethiopia

[2]Department of Civics and Ethical Education, College of Sciel Sciences and Humanities, Debre Markos University, Debre Markos, Ethiopia

*Corresponding author's Email: derb_tefera@dmu.edu.et , derbtefera@gmail.com

**አጠቃሎ**

የገናና ታሪክ ባለቤትና በቁጥር የመጀመሪያውን ወይም ሁለተኛውን ቦታ ይይዛል ተብሎ የሚገመተው የአማራ ህዝብ ለማያባራ የብሄርተኞች ጥቃት ለምን እንደተጋለጠና ችግሩን መቀልበስ እንዴት እንደተሳነው በውል አይታወቅም፡፡ የዚህ ጥናት ዓላማ እነዚህን ችግሮች መመርመርና ለጥያቄዎቹ መልስ ማፈላለግ ነው፡፡ ለዚህም ይረዳ ዘንድ ተዛማጅ የሆኑ የምርምር ስራዎችና የቃለ-መጠይቅ መረጃዎች በብቃትና በጥንቃቄ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ የጥናቱ ግኝት እንደሚያሳየው የአማራን ህዝብ ለብሄርተኞች ሁለንተናዊ ጥቃት ያበቁት መንስዔዎች ዘርፈ ብዙና በጊዜ ርዝመት እየተወሳሰቡ የመጡ ናቸው፡፡ የብሄርተኞችን አነሳስ፣ ዓላማና እንቅስቃሴ ተገንዝቦ ገና ከጅምሩ ተመጣጣኝ ለሆነ የፖለቲካና ወታደራዊ ትግል አለመዘጋጀት፤ የትውልድ ክፍተት፤ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ድቀት፤ ከምንም በላይ ደግሞ አማራ በብሄርተኞች ዘመን ከዜግነት ፖለቲካ ውጭ ሌሎች አማራጮችን ማማተር አለመቻሉ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ በብሄር ፌደራሊዝሙ አማራ አለመወከሉና ክልሉ የአማራ ማንነት በሌላቸው እና በአቅመ-ቢስ አማራዎች መመራቱ፤ የአማራ ጥቃት ሥርዓታዊና መዋቅራዊ መሆኑ፤ የአማራ ህዝብ ችግሩን ለመቀልበስ የሚያደርገውን ትግል ፈታኝ አድርጎበታል፡፡አማራ ከዚህ አዞሪት ይወጣ ዘንድ ከላይ የተጠቀሱትን የታሪክ ግድፈቶች አርሞ ሁሉን አቀፍ ትግል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

**ቁልፍ ቃላት** አማራ፤ ህዝብ፤ ታሪካዊ፤ ብሄርተኛ፤ ኅብረ-ብሄራዊ፡፡

**Abstract**

It is not precisely known as to why the Amhara people, the owner of a great history and the one which is believed to be the first or the second in population size in the country, exposed for continual ethno-nationalists attack and failed to repulse it. This study aims to investigate these gaps and come up with relevant answers. To this end, related research works and oral

informations are consulted and adequately used. The findings show that the crux of the matter which exposed the Amhara people for incessant ethno-nationalists attack emanated from multifarious causes and become complicated through time. Failure to prepare for political and military struggle understanding the very rise, objective and movement of ethno-nationalists; generation gap; economic and cultural attenuation, above all the failure of Amhara in searching for alternatives other than citizen politics at the times of ethno-nationalists are the main ones. Besides, the fact that Amhara was not properly represented in the ethnic federalism; the Amhara region was long administered by non-Amharas and incompetent Amharas; the attack on Amhara is systematic and structural made the Amhara's struggle in dealing with the problems more difficult. For the Amhara people to be free from these vicious problems, it should have to learn from its historical flaws and embark on an all-encopmassing struggle.

## **መግቢያ**

**ፋሺስት ጣሊያን እኤአ ከ1936 እስከ 1941 በኢትዮጵያ ቆይታው የፖለቲካል አስተዳደሩን ያዋቀረው አነሰም በዛም ቋንቋን ወይም ዘውግ ብሄርን ዋና መስፈርት አድርጎ ነው፡፡ በተግባር ያልተተረጎመ ቢሆንም በአስተዳደር ግዛቶቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያደርግ ድንጋጌም አውጥቶ ነበር፡፡ ይህም የኢትዮጵያን ህዝብ በብሄር፤ በባህልና በእምነት ማንነት በመከፋፈል** (ባህሩ ፣1983፣172፣177፡ Baheru ፣*2008a*፣*86;* González-Ruibal, 2010, 6 *)*፣ **ለቅኝ ግዛቱ እውን መሆን ስጋት ናቸው ባላቸው የአማራ ህዝብና ኦርቶዶክስ ኃይማኖት** (ሙሉቀን ተስፋው፣2008) **ላይ የማንነት ጥቃት ለመቀስቀስ ምቹ ሁኔታን ሳይፈጥርለት አልቀረም፡፡ የዚህ ጥሩ ማሳያ አንዳንድ ብሄረሰቦችና ጥቂት የእስልምና እምነት ተከታዮች የጣሊያን ተባባሪ መሆናቸው ነው** (González-Ruibal, 2010, 21; Ezekiel, 2002, 76,78)፡፡ **በዚህም ይሆናል የብሄርተኝነት እሳቤ በኢትዮጵያ የተዘራው በጣሊያን የይዞታ ዘመን መሆኑን የምርምር ስራዎች ይጠቅሳሉ** (Vaughan ፣ 2003፣119-122 ፣ Teshome ፣ 1980/81 ፣ 70 ፤ **ባህሩ**፣1983፣273)፡፡

**ይሁንና በጣሊያን የይዞታ ጊዜ ቀርቶ ከነፃነት በኂላም እንኳ ብዙዎቹ በቁጥር ታላላቆቹም ሆኑ አናሳዎቹ የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች አሁን በያዙት የማንነት ስያሜ አይታወቁም ነበር፡፡ ዳንኤል ክንዴ እንደጠቀሰው ከ30 ዓመት በፊት የአሁኑ ኦሮሞ የሚታወቀው ሜጫ፤ ቱለማ፤ አሩሲ ፤ ቦረና ወዘተ ስያሜወች ነበር፡፡ ከ20 ዓመት በፊት ትግሬም ማንነቱን**

የሚገልፀው፤አጋሜ፤ እንደርቱ፤ ሺሬና በመሳሰሉት መጠሪያዎች ነበር፡፡ በተመሳሳይ አማራም ከ10 ዓመት በፊት ጎንደሬ፤ ጎጃሜ፤ ቡልጌ፤ ሳይንቴ፤ ወሎዬ ነኝ ይል ነበር (Daniel ፤2003፣183)፡፡ የዳንኤል ምርምር የታተመበትን (እኤአ 2003) እንደ መነሻ ወስደን ወደ ኋላ ስናሰላ ኦሮሞ፤ ትግሬና አማራ የሚሉት ስያሜዎች የማንነት መጠሪያ የሆኑት እንደ ቅደም ተከተላቸው ከ1970ዎቹ፤ 1980ዎቹ እና 1990ዎቹ የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ወዲህ ነው፡፡ ቀደም ሲል በአካባቢያቸው ስያሜ ይጠሩ የነበሩ የማህበረሰብ ክፍሎች በድህረ ጣሊያን የብሄር ስም መያዛቸው በኢትዮጵያ የዘውግ ብሄርተኝነት አስተሳሰብ የተዘራው እኤአ ከ1936 እስከ 1941 ባለው የጣሊያን የወታደራዊ ይዞታ ጊዜ ነው የሚለውን ሃሳብ ያጠናክርልናል፡፡ (Vaughan ፣ 2003፣165፤ Bahru ፣2008b፣44፣Brietzke፣1995፣20)፡፡

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግስት ጨቋኝ መሆኑ ብዙዎችን ቢያስማማም የብሄር ጭቆና ስለመኖሩ እስከ አሁን ድረስ ስምምነት ላይ አልተደረሰም፡፡ በመጨረሻው የንጉሱ ዘመነ መንግስት ልሂቃን በተለይ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የብሄር ጭቆና አለ የለም በሚል ሰፊና የከረረ ክርክር ያደርጉ ነበር (Abdul ፤2010፣101፤Bahru ፤2014፤199-200)፡፡ ምንም እንኳን አጀንዳው መቋጫ ባያገኝም የክርክር ሂደቱ አያሌ የኦሮሞና የትግሬ ብሄርተኛ ወጣቶችን ወልዶና አሳድጎ ወደ ጫካ እንዳስገባ የብሄር ነፃ አውጪ ግንባሮች አፈጣጠር አስረጂ ነው፡፡ በግምት እኤአ ከ1965 በፊት የጎላ የኦሮሞ ብሄርተኝነት ፍላጎትም ሆነ ስሜት አልነበረም፡፡ በተጠቀሰው ዓመት ግን ቱለማ ሜጫ የራስ አገዝ መረዳጃ ማህበር ማንነትን መሰረት አድርጎ ተቋቋመ (Keller፣1995፣627)፡፡ በመቀጠልም የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር (ኦነግ) እኤአ በ1973 ተመሰረተ (Ibid.,628)፡፡ በተመሳሳይ የትግራይ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ህብረትና ሌሎች ህቡዕ አደረጃጀቶች ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ፡፡ ከዚያም የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጪ ግንባር (ትህነግ) የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ሪፐበሊክን የመመስረት ዓላማ አንግቦ ከሁለት ዓመት በኋላ እኤአ በ 1975 ተመሰረተ (Bennett ፣ 1983 ፣9 6 ፤ Vestal፣1999፣Viii፣Paulos፣ 2003፣13)፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ በጨቋኝነት ከተፈረጀው የአማራ ብሄር አብራክ የወጡ ልጆች፣ የብሄር ጥያቄን የሚደግፉትም፣ የማይደግፉትም ይሳተፉ የነበረው የኢትዮጵያ ህዝቦች አንድነት ፓርቲ (ኢህአፓ)፣ መላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) እና በመሳሰሉት ህብረ-ብሄራዊ ድርጅቶች ውስጥ ነበር፡፡ በዚህም

የነበራቸው ተሳትፎ ከአመራር ቦታ በጣም የራቀ ነበር። ለምሳሌ ያክል የኢህአፓ የአመራር ቦታ የተያዘው ሊጣጣም በማይችል ሁኔታ በኤርትራና ትግራይ ተወላጆች ነበር (Halliday and Molyneux፣1982፣11)።

የብሄር ስብጥሩን በትክክል ማወቅ ባይቻልም፤ ንጉሳዊ አገዛዙን የተካው ደርግ ኅብረ-ብሄራዊ መሆኑ ይገለፃል (Markakis፣1989፣123-124)።

በመጀመሪያዎቹ ዓመታት የኦሮሞ የበላይነት ይታይበት እንደነበር መረጃዎች ቢያሳዩም (Vaughan፣2003፣149) የደርግ መንግስት ሁሉንም ኢትዮጵያዊያን አካታች እንደነበር ይታመናል። ደርግ "National Democratic Revolution" በሚለው የፖለቲካ ፕሮግራሙ ለኢትዮጵያ ብሄሮች ብዝሃነት፤ በሶሻሊስት መርህ ራስን የማስተዳደርና ሰለ ቋንቋ መብት እውቅና ሰጥቷል (Beken፣2015፣152)። ይህ በእንዲህ እንዳለ ከላይ የተጠቀሱት የብሄር ግንባሮች ትግላቸውን ቀደም ሲል በተፈጠሩበት የብሄር መልክና ቅርፅ ቀጥለዋል። ምንም እንኳ የኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢህዴን)፤ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መኮንኖች አብዮታዊ ንቅናቄ (ኢዴመአን)፤ የኤርትራ ህዝብ ነፃ አውጪ ግንባር እና የመሳሰሉት ኅብረ-ብሔራዊ ግንባሮች ተጋድሎ ከፍተኛ ቢሆንም (ባህሩ፣1983፣276-277) ደርግን የተካው ህውሃት መራሹ የኢህአዴግ መንግስት የብሄር ቅርፅ መያዙና ብሄርተኞች በተለይ ህውሃትና ኦነግ በሽግግር መንግስቱ ወሳኝ የስልጣን ቦታ መቆጣጠራቸው (Vaughan፣2003፣28)፤ የኅብረ-ብሔራዊ ግንባሮችን የተጋድሎ ዋጋ አደብዝዞታል። በሂደትም ኢትዮጵያዊነትን የሚያቀነቅኑ ህዝቦችን በተለይም የአማራ ህዝብን ለተለየ ጥቃት አጋልጦታል።

የምርምር ስራዎች እንደሚያሳዩት በብሄርተኞቹ የትግል ጉዞና የአገዛዝ ዘመን የአማራ ህዝብ የተለያየ መልክና ቅርፅ ያለው ጥቃት ደርሶበታል (ሙሉቀን፣2008)። በተለይ ህውሃት መራሹ የኢህአዴግ መንግስት ሥልጣን ከያዘበት እኤአ ከ1991 ጀምሮ የአማራ ህዝብ የሰው ልጅ ባሳለፈው የታሪክ ዘመኑ ይፈፀማሉ ተብለው የማይታሰቡ ኢሰብአዊ ግድያ፤ የኢኮኖሚ ውድመት፤ ግርፋት፤ እስራት፤ መሰወር፤ ስደትና ወከባ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ፖለቲካ ማግለልን ጨምሮ የማንነትና የመሬት ዘረፋ ሰለባ ሆኗል፤ እየሆነም ነው። በችሮታ በተሰጠው የአማራ ክልል የሚኖረው ህዝብ በኢኮኖሚ አሻጥር ለድህነት እንዲጋለጥ እና ክልሉ ከማንኛውም ክልሎች በተለየ መልኩ በመሰረተ-ልማት ወደ ኋላ እንዲቀር ብዙ ስራ ተሰርቷል። ከክልሉ ውጭ የሚኖረው

የአማራ ህዝብ በተለይ የጎላ የማንነት ጥያቄ አንስቶ እስከአሁን ድረስ ምላሽ ያላገኘው የወልቃይት፤ ጠገዴ፤ ጠለምት፤ ራያ፤ መተከልና ደራ አማራ ከግድያውና የኢኮኖሚ አሻጥር ባለፈ ማንነቱን እንዲቀይር ካልሆነም ርስቱን ለቆ እንዲሰደድ ተደርጓል። እነዚህ ግፎች በታቀደና በተደራጀ መልኩ እየተፈፀሙ ሳለ አማራን እወክላለሁ የሚለው ኢህዴን-ብአዴን-አዴፓ እንዲሁም የአሁኑ የአማራ ብልፅግና እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ይህን የአማራ ግፍ በቸልታ ሲያልፈው ቆይቷል (ከላይ የተጠቀሰው)። ህውሃት ከማዕከላዊ መንግስቱ ከተባረረ ወዲህ የአማራን ህዝብ ግፎች የመቃወም አንዳንድ ሙከራዎች ቢታዩም በቀጣይነት አልተፈፀሙም። በታሪክ አጋጣሚ በመላው ኢትዮጵያ ተበትኖ ለሚገኘው የአማራ ህዝብ ይቅርና በችሮታ ከተሰጠው የአማራ ክልል ተቆርሰው በተወሰዱትና የጎላ የአማራ የማንነት ጥያቄ በሚነሳባቸው ወልቃይት፤ጠገዴ፤ ጠለምት፤ ራያ፤ ደራ እና መተከል በአማራ ላይ ለሚፈፀሙ ግፎች እንኳ እንደአጠቃላይ የክልሉ መንግስትና ህዝብ በተለይ ደግሞ በኩታ ገጠም ያለው የአማራ አካባቢያዊ አስተዳደርና ህዝብ ስደተኞችን ከመቀበል (እንደየሁኔታው የሚለያይ ሆኖ) ባሻገር አፀፋዊ ምላሽ ለመስጠት ሲንቀሳቀሱ አልታዩም (Bahru ፣ 2008a ፣ 383)። በዚህም ምክንያት ይሆናል በአማራ ህዝብ ላይ የሚፈፀሙ ግፎች በመላው ኦሮሚያ፤ ቤንሻንጉል፤ ወልቃይት፤ ጠገዴ፤ ጠለምት፤ ራያ፤ በአጣየና አካባቢው፤በደራና በመሳሰሉት ከጊዜ ወደ ጊዜ በስፋትና በግዝፈት እየጨመሩ እንጂ እየቀነሱ አይደለም።

ካለፈ ታሪኩ የምንረዳው አማራ ለረጅም ዘመናት መንግስታዊ ህዝብ መሆኑን ነው። አገር አቅንቶ፤ መንግስት መስርቶ፤ክብረ መንግስትና ፍትሃ ነገስት የመሳሰሉ ህገ-መንግስቶችን ቀርፆ፤ በመንግስታዊ ስርዓት ያስተዳደረና የተዳደረ ህዝብ ነው (Levine ፣ 2012፣51)። የውጭ ወራሪ ሲመጣ እምቢ ላገሬ፤ እምቢ ለነፃነቴ ብሎ ዘምቶ ወራሪዎችን አሳፍሮ የመለሰና ነፃነቱን አስጠብቆ የኖረ ህዝብ ነው (Bahru ፣ 2008a፣ 383-384)። በብሄርተኞች የአገዛዝ ዘመን ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ደህንነታቸውንና ክብራቸውን አስጠብቀው በሚኖሩባት አገር የገናና ታሪክ ባለቤትና በቁጥር የመጀመሪያውን ወይም ሁለተኛውን ቦታ ይይዛል ተብሎ የሚገመተው[1] የአማራ ህዝብ ለብሄርተኞች

[1]እኤአ በ1984 የተከናወነው የህዝብና ቤት ቆጠራ ሁሉንም የአገሪቱ ክፍል በተለይ የሰሜኑን የአገሪቱ ክፍል ያላካተተ በመሆኑ በኦሮሞ ህዝብ በትንሺ

ጥቃት ለምን ተጋለጠ? ችግሩን መቀልበስ እንዴት ተሳነው? የሚሉት ጥያቄዎች መልስ ይሻሉ። የዚህ ጥናት ዓላማ ለነዚህና ተዛማጅ ጥያቄዎች መልስ ማፈላለግ ነው።

የአማራ ህዝብ ከሶስት አስርት ዓመታት በላይ ላስቆጠረ ሁለንተናዊ ጥቃት እንዲጋለጥም ሆነ ሙሉ አቅሙን ተጠቅሞ መቀልበስ እንዳይችል ያደረጉት ምክንያቶች መነሻቸው ረዘም ያለ ዕድሜ ሊኖረው ስለሚችል፣ ይህ ጥናት ቢያንስ በሶስት መንግስታት ዘመን የተከናወኑ ታሪካዊ ክስተቶችን ለመዳሰስ ይሞክራል። ለአጠናን ዘዴ ያመች ዘንድ፣ መግቢያ፣ የፅንሰ-ሃሳብና ንድፈ-ሃሳብ አወቃቀርና የጥናቱ ንድፍና ዘዴ የሚሉ ንዑስ ርዕሶች በመጀመሪያ ቀርበዋል። የጥናቱ ግኝት የጊዜ ቅደም ተከተልን በመጠቀም በሶስት ንዑስ ርዕሶች ማለትም ቅድመ አብዮት፣ የወታደራዊው አስተዳደር ዘመንና የብሄርተኞች የአገዛዝ ዘመን ሥር ተዳሷል። በመጨረሻም ምንም እንኳን እያንዳንዱ ንዑስ ርዕስ ከአንድ አንቀፅ ያልበለጠ መደምደሚያ ቢኖረውም፣የጥናቱ አብይ መደምደሚያ ግን ራሱን በቻለ ንዑስ ርዕስ ቀርቧል።

**የፅንሰ-ሃሳብና ንድፈ-ሃሳብ አወቃቀር**

በዚህ ጥናት ውስጥ ቁልፍ ከሆኑ ፅንሰ-ሃሳቦች አንዱ አማራ ነው። ይህ ፅንሰ-ሃሳብ በዚህ ጥናት የሚወክለው የአማራ ማንነት ያለውን የማህበረሰብ ክፍል ብቻ ሳይሆን ሌሎች ንዑስ ማንነት ያላቸውን እንደ አገው፣ አዊ፣ አርጎባ ወዘተ. የመሳሰሉትን ጭምር ነው። ይህም የሆነው ከብዙ በጥቂቱ በሁለት ዓበይት ምክንያቶች ነው። አንደኛ እነዚህ ብሄረሰቦች ለረጅም ዘመናት የአማራ ታሪክ፣ ባህል (እምነት፣ ቋንቋና የመሳሰሉትን) ተጋሪ ከመሆናቸው የተነሳ የአማራ ስነ-ልቦና የተላበሱ ናቸው። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በብሄርተኛው የትግል ጉዞና አስተዳደር ዘመን የአማራን ግፍና መከራ እኩል ተቋዳሺ የሆኑት በአማራ ስም ነው። ሁለተኛው ፅንሰ-ሃሳብ ህዝብ ነው። ባህሩ እንደሚያስረዳው ህዝብ የሚለው ቃል ለቅይጥ ማህበረሰብ የጋራ መጠሪያ የሚያገለግል ስለሆነ(ባህሩ ፣2011፣77-78) በዚህ ምርምር የተካተቱ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች በጋራ የአማራ ህዝብ ተብለው ይጠራሉ።

ይህ ጥናት በሚያካትታቸው የአስተዳደር ዘመናት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ገዢ የነበሩ ፅንሰ-ሃሳቦች ማለትም የመደብ ጭቆና (Class Oppression)፣ የብሄር ጭቆና

ቁጥር ልዩነት ተቀድሞ ሁለተኛ ደረጃ የያዘው የአማራ ህዝብ በትክክልና በተሟላ ሁኔታ የህዝብ ቆጠራ ቢደረግ የመጀመሪያ ደረጃ እንደሚይዝ የቆጠራው ክፍተቶች ያሳያሉ።Central Statistical Authority, The 1984 Population and Housing Census of Ethiopia፣ an alytical report at national level,Addis Ababa, 1991. ተመልከት።

(Ethnic Oppression) እንዲሁም የብሄርተኛው ዋና ማታገያ የነበረው አብዮታዊ ዴሞክራሲ (Revolutionary Democracy) የመነጨት ከሶሻሊዝም ርዕዮት ስለሆነ፤ በነዚህ እሳቤዎች ምክንያት የተከሰቱ የአማራ ህዝብ ውጣ ውረዶችን ከማርክሲስት-ሌኒኒስት ንድፈ-ሃሳብ አንፃር ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡

**የጥናቱ ንድፍና ዘዴ**

ይህ ጥናት በዓይነታዊ የምርምር አቀራረብ ተከናውኗል፡፡ የአማራ ህዝብ በብሄርተኞች የትግል ጉዞና የአገዛዝ ዘመን ለፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊ፤ ወታደራዊ፤ ማህበራዊና ባህላዊ በጎም ሆነ መጥፎ ተፅዕኖዎች ተጋላጭ መሆኑ እሙን ነው፡፡ ስለሆነም ይህንን ያለፈ ክስተት ለመረዳት የሚያስችለው ታሪካዊ የምርምር ንድፍ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ለጥናቱ የዋሉ አፋዊ መረጃዎች ወሳኝ ንሞና ዘዴን ከዚያም ጠቋሚ ወይም ተያያዥ ንሞና ዘዴ በመጠቀም ተሰብስበዋል፡፡ የመረጃ ስብሰባ ስራው የናሙና መጠንን ሳይወስን የመረጃ ድግግሞሺ እስካጋጠመ ድረስ ተከናውኗል፡፡ ጥናቱ በዋናነት ሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተጠቅሟል፡፡ እነዚህም የምርምር ፅሁፎች ፍተሻና ቃለ-መጠይቅ ናቸው፡፡ ተአማኒነት ያላቸውን መረጃዎች የማግኘት ዕድሉን ከማስፋት ባለፈ መረጃዎችን በማመሳከር ትክክለኛነት የሚጎድላቸውን የመለየትና የማስወገድ ስራ ተሰርቷል፡፡ ከዚያም በፈርጅ በፈርጁ ተለይተው የጭብጥና የይዘት ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡ በቃለ-መጠይቅ ለተሰበሰቡ መረጃዎች ደግሞ ትረካዊ ትንተና ተፈፅሟል፡፡ በዚህ ሂደት መረጃዎች ተገምግመውና ተተንትነው ከተለዩ በኋላ ትክክለኛ ትርጉማቸውን በመስጠት ምንም ሳይጨመር፤ ምንም ሳይቀነስ የፅሁፍ ስራ ተሰርቷል፡፡

**ቅድመ-አብዮት**

ቀዳማዊ ኃይለ ሥለሴ የዘመናዊ ኢትዮጵያ ግንባታ ግንባር ቀደም የታሪክ ባለቤት መሆን ይፈልጉ እንደነበር ተቆርቋሪ ኢትዮጵያን ጭምር ይመሰክራሉ (Levine፣1961፣11)፡፡ ለዚህም ይሆናል በድህረ ነፃነት ኢትዮጵያ በጣሊያን ወታደራዊ ይዞታና ከዚያ በፊት የነበሩ ጅምር ዘመናዊ ተቋማትን ከማሳደግና ከማስፋፋት በተጨማሪ አዳዲስ ተቋማትን በመመስረትና ዘመናዊ አሰራርን በመዘርጋት ረገድ ቀላል የማይባል ስራ ተሰርቷል፡፡ ት/ቤት፤ ሆስፒታል፤ ባንክ፤ የመገበያያ ገንዘብ፤ የአየር ትራንስፖርት፤ ቴሌኮሙኒኬሺን፤ ዘመናዊ መጓጓዣ ወዘተ. እንዲመሰረቱና እንዲስፋፉ ተደርጓል፡፡ የሲቪል አስተዳደሩን ለማዘመን ተሞክሯል፡፡ ፍፁማዊ አገዛዙን ዕውን ለማድረግ ጠቅላይ ግዛቶች፤ በመገናኛ እጥረት የሚፈጠሩ ችግሮች እንዳሉ ሁኖ፤ በጠንካራ የተማከለ

አስተዳደር ስር ተካተዋል፡፡ ጠንካራ ዘመናዊ የፀጥታ ሃይልም ተገንብቷል፡፡ የገንዘብ ፍሰቱም የተማከለ እንዲሆን ተደርጓል (ባህሩ፣1983፣220-222) በአጠቃላይ በብዙ መስኮች በተመዘገበው አንፃራዊ ዕድገት ምክንያት ከ1950ዎቹ እስከ 1970ዎቹ ያሉት ዓመታት የዘመነ ዘመናዊነት ጊዜያት እንደነበሩ የምርምር ስራዎች ያሳያሉ (Eyayu ፣1994፣26) ፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ በንጉሱ ሥርዓት ላይ የተለያየ መልክና ቅርፅ ያላቸው ተቃውሞዎች ተሰብቀዋል፡፡ እነዚህን ተቃውሞዎች ለአማራ ህዝብ ካላቸው ጥቅምና ጉዳት አንፃር ለማብራራት ያመች ዘንድ በመንስኤዎቻቸው ለሁለት ከፍለን እናያቸዋለን፡፡ የመጀመሪያዉ መንስኤ የንጉሱ አስተዳደር ጥቂት ግለሰቦች በብዙሃኑ ድሃ ኢትዮጵያዊያን ትካሻ ላይ የሚመሩትን የተንደላቀቀ ህይወት የሚያስቀይር ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ለውጥ ማምጣት አልቻለም የሚል ነው፡፡ ይህ አመክንዮ የመደብ ጭቆናን የሚገልፅ ስለሆነ አቀንቃኙ የጭቁኑን የአማራ ህዝብ ጉዳትና ብሶት እንደማንኛውም ጭቁን የኢትዮጵያ ህዝብ በእኩል ያያል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የንጉሱ ሥርዓት የብሄሮችን ማንነት ደፍጥጧል የሚል ነው፡፡ የብሄር ጭቆና አቀንቃኙ ኃይል የአማራ ህዝብ ጨቋኝ እንጂ እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ህዝብ ተጨቋኝ መሆኑን አይቀበልም፡፡ ከነዚህ ተፃራሪ እሳቤዎች የመነጩ ተቃውሞዎችን ሁሉ ለማብራራት ጊዜና ቦታ ስለማይፈቅድ፤ ለዚህ ጥናት ቅርብ የሆኑት ላይ እናተኩራለን፡፡

የገዢው መደብ ጭቆና ያንገፈገፋቸው የማህበረሰብ ክፍሎች በተለያየ ጊዜና ቦታ በንጉሱ አገዛዝ ላይ ተቃውሞ ሰብቀዋል፡፡ ገበሬዎች ለኢኮኖሚያዊ ፍትህ፤ ምሁራን ፍትህና እኩልነት ለሰፈነበት አዲስ ሥርዓት፤ የገዢው መደብ አባላት ስርዓቱን ለማሻሻል ታግለዋል (ባህሩ ፣1983 ፣ 220)፡፡ በምሁራንና የገዢው መደብ አባላት ከተሰበቁ ተቃውሞዎች ግንባር ቀደም ተጠቃሺ የሚሆነው እኤአ በ1960 የተደረገው የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ነው፡፡ የመፈንቅለ መንግስቱ አነሳሽ ሃሳብ ከላይ እንደተጠቀሰዉ የንጉሱ አስተዳደር ጥቂት ግለሰቦች በብዙሃኑ ድሃ ኢትዮጵያዊያን ትካሻ ላይ የሚመሩትን የተንደላቀቀ ህይዎት የሚያስቀይር ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ለውጥ ማምጣት አልቻለም የሚል ነው (Yohannis ፣ 1980/81፣4)፡፡ በመሆኑም ለ3000 ዓመት ነፃነቷን ጠብቃ ከኖረችው ሃገራችን ኢትዮጵያ ይልቅ በቅርብ ጊዜ ነፃነታቸውን የተጎናፀፍት የአፍሪካ አገሮች ፈጣን እድገት እንዳስመዘገቡ በመጥቀስ አገራችንን ወደ

ቀድሞው ገናናነቷ ለመመለስ ለውጥ አስፈላጊ መሆኑን የመፈንቅለ መንግስቱ አቀናባሪዎች በምክንያት አቅርበዋል (ባህሩ፣1983፣223)፡፡ ዋና አቀነባባሪዎቹ ወንድማማቾቹ ብርጋዲየር ጄኔራል መንግስቱ ነዋይና ገርማሜ ነዋይ እንደቅደም ተከተላቸው የወታደሩንና የምሁሩን ክፍል ይወክላሉ፡፡ ይሁን እንጂ መፈንቅለ መንግስቱ በደንብ የታቀደ ስላልነበረ የመንግስት ኃይሎች የበላይነት ሲወስዱ አቀነባባሪዎቹ በማግለያ ቦታ ያስቀመጧቸውን ሚኒስትሮችንና የስርዓቱን ቁንጮዎች ከረሸኑ በኋላ ከአዲስ አበባ ውጭ ባካሄዱት የተኩስ ልውውጥ ገርማሜ ነዋይ ዝቋላ አካባቢ ሲሰዋ፤ ሌተናል ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ እራሱን ገድሏል፡፡ ብርጋዲዮር ጄኔራል መንግስቱ ነዋይ ደግሞ ቆስሎ ከተያዘ በኋላ በስቅላት ተቀጥቷል (ባህሩ ፣1983፣208፣222-224)፡፡ በዚህም የመፈንቅለ መንግስቱ ሙከራ በአጭሩ ተገትቷል፡፡ ሆኖም ግን ለዘመናት የማይደፈርና የማይገሰስ ተደርጎ ይታሰብ የነበረውን የዘውዱን ስርዓት ሊቀየር እንደሚችል አመላክቷል፡፡ ይህም በሥርዓቱ ላይ ከፍተኛ የፖለቲካ ኪሳራ አስከትሎበታል፡፡ የኋላ የኋላ የንጉሱ ራስ ምታት የሆነው የተማሪዎች ንቅናቄና ሌሎች ተቃዋሚዎች እንዲፈጠሩ መሰረት ጥሏል፡፡ በተጨማሪም የለውጡ ተዋናኞችም ሆኑ የመንግስት ታማኞች ማህበራዊ መሰረት በአብዛኛው የአማራ ህዝብ በመሆኑ ከሁለቱም በኩል የደረሰው ሰብአዊ ጉዳት ከማንም በላይ በአማራ ምሁራንና ልሂቃን ላይ ትልቅ ኪሳራ ማስከተሉና በወደፊቱ የአማራ ህዝብ ዕጣ ፈንታ ላይ ጉልህ የሆነ ተፅዕኖ ማሳረፉ አያጠያይቅም፡፡

የመፈንቅለ መንግስቱ ሙከራ በአፋጣኝ ድጋፍ የተቸረው ከዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ነበር፡፡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በዕለቱ አደባባይ በመውጣት ድጋፋቸውን ገልፀዋል፡፡ ከመፈንቅለ መንግስቱ ሙከራ በኋላም የንጉሱ ሥርዓት ዋና ተቃዋሚ ኃይል ሆነው ወጥተዋል፡፡ ተማሪዎች መሬት ላራሹንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች አንግበው አደባባይ በመውጣትና ትምህርት በማቆም ሥርዓቱን ሞግተዋል፡፡ በተቃውሞ ሂደቱም አያሌ የወደፊት የአገር አለኝታ ሊሆኑ የሚችሉ ተማሪዎች እንደተሰው ጥናቶች ያስረዳሉ (Yohannis ፣1980/81፣2)፡፡ እኤአ በ1950ዎቹ እና በ1960ዎቹ ከግማሽ በላይ የሚሆነው የዩኒቨርሲቲ ተማሪ አማራ ስለነበር (Balsvik፣1985፣44)በተማሪዎች ንቅናቄ በቀጣይነት በተሰበቁ ተቃውሞዎች ምክንያት ከተመዘገበው ለውጥም ሆነ ሰብአዊ ጉዳት የአማራ ህዝብ ትልቁን ድርሻ ይወስዳል፡፡

ሁለተኛው የተቃውሞ መንስኤ የብሄር ጭቆና ነው። ምንም እንኳ የብሄር ጥያቄ ዋና አጀንዳ የሆነው ጉዳዩ የተማሪዎች ፖለቲካ ሆኖ ጎልቶ ከወጣበት እኤአ ከ1969 ጀምሮ ቢሆንም፤በብሄር ስሜት የተቀሰቀሱ ህዝባዊ አመፆችና ተቃውሞዎች ከነፃነት ጊዜ ጀምሮ ተከስተዋል። እኤአ የ1941-1943 የወያኔ አመፅ፤ እኤአ 1964-1970 የባሌ ገበሬዎች አመፅና እኤአ ከ1965 ጀምሮ የሜጫ ቱለማ ራስ አገዝ የመረዳጃ ማህበር እንቅስቃሴዎች ተጠቃሽ ናቸው(Bahru፣2014፣187-188 ፣ Beken ፣ 2015 ፣ 151)። ስለሆነም በብሄር ጭቆና ስሜት የተሰበቁ ሁለት የትጥቅ ትግሎችንና ሁለት ሰላማዊ ተቃውሞዎችን እንደ ክንውን ቅደም ተከተላቸው ከዚህ በታች በአጭሩ እንዳስሳለን።

በትጥቅ ትግል ጎራ ከሚመደቡት የወያኔና የባሌ ገበሬዎችን አመፅ እናገኛለን። የወያኔና የባሌ ገበሬዎች አመፅ የኢኮኖሚ ብዝበዛና የፖለቲካ ጭቆና(የአማራ የበላይነት) የጋራ አመክንዮ አድርገው የተነሱ ሲሆን በተጨማሪ ኃይማኖትን እንደማታገያ መሳሪያ ተጠቅመውበታል (ባህሩ፣ 1983 ፣ 226 ፤ Vestal ፣ 1999፣XV)። ወያኔ ጣሊያን ትቶት የሄደውን መሳሪያ የመጠቀም ዕድል ሲኖረው የባሌ ገበሬዎች አማፂያን በጦር መሳሪያና በሰው ሃይል ስልጠና የውጭ ኃይል (የሶማሊያ) ድጋፍ ነበረው። አማፂያኑ የነበራቸው ሌላው ምቹ ሁኔታ አመፆቹ የተሰበቁበት አስተዳደር መገኛ ነው። ልዩነታቸው የተጠበቀ ሆኖ የአመፆቹ መነሻ ጠቅላይ ግዛቶች ከማዕከላዊ መንግስቱ መቀመጫ በርቀት የሚገኙ በመሆናቸው በአንፃራዊ ልል መንግስታዊ አስተዳደር ይታይባቸው ነበር። ለዚህም ይሆናል አማፂያኑ፣ ምንም እንኳ በመጨረሻ ተሸናፊ ቢሆኑም፤ የመንግስትን ኃይል በጥሩ ሁኔታ ለመፈታተን ችለዋል (ባህሩ፣1983፣226-229፤Vestal፣1999፣XV)። እነዚህ አመፆች የገበሬ አመፅ ከመሆናቸው የተነሳ አማፂያኑ በመሬታቸውና በላባቸው ፍሬ ላይ የተጋረጠውን ጫና ከማቅለልና የውሥጥ አስተዳደር ነፃነት ከማረጋገጥ ያለፈ ዓላማ አልነበራቸውም። ለዚህም ይሆናል መንግስት ከከሸፈው መፈንቅለ መንግስት አቀነባባሪዎች በተፃራሪ ለባሌ ገበሬዎች አመፅ መሪ ዋቆ ጉቱ፤ ምንም እንኳ አገሩን ከድቶ ከውጭ ኃይል ጋር ትብብር የፈጠረ መሆኑ ቢታወቅም፤ ምህረት አድርጓል (ባህሩ ፣ 1983 ፣ 284)።

እኤአ ከ1960ዎቹ ጀምሮ በሰላማዊ ትግል የብሄር ጭቆናን ካቀነቀኑ ሃይሎች የሜጫ ቱለማ ራስ አገዝ የመረዳጃ ማህበርና የተማሪዎች ንቅናቄ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። የሜጫ ቱለማ ራስ አገዝ የመረዳጃ ማህበር ከስሙ እንደምንረዳው ማህበራዊና

ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት የተመሰረተ ማህበር ነው (ባህሩ፣1983፣ 273-274፤Keller፣1995፣627)። ሆኖም ግን የኋላ ኋላ በአንድም ሆነ በሌላ የኦሮሞ ብሄርተኝነት ተወልዶ እንዲጎለምስ በጊዜ ሂደትም የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር እንዲመሰረትና ጨቋኝ ባለው የአማራ ህዝብ ላይ ጦርነት እንዲሰብቅ የሰብአዊ፤ ርዕዮትና የፋይናንስ ድጋፍ ከማድረግ ባለፈ በንጉሱ ሥርዓት ላይ በማንነት የተቃኘ ተቃውሞ ያሰማ ነበር (ባህሩ፣1983፣273-274 ፤ Keller ፣ 1995 ፣ 627 ፣ Baheru ፣2014፣ 193-194)።

ይሁንና የብሄር ጥያቄ በግልፅ የተቀነቀነው የከሸፈውን መፈንቅለ መንግስት ዱካ በተከተለውና የንጉሱን መንግስት መሰረት ባናጋው የተማሪዎች ንቅናቄ ነበር። የንቅናቄው ተሳታፊዎች ሁሉንም የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች የሚወክሉ ነበሩ። ሆኖም ግን ከላይ እንደተገለፀው እኤአ በ1950ዎቹ እና በ1960ዎቹ ከግማሽ በላይ የሚሆነው የዩኒቨርሲቲ ተማሪ አማራ በመሆኑ (Balsvik፣1985፣44) በንቅናቄው ውስጥም የአማራ ተሳትፎ ከፍተኛ እንደነበር ይገመታል። ያም ሆኖ ግን ተማሪዎች የአማራ የበላይነት ይንፀባረቅበታል ተብሎ በሚወቀሰው የዘውዳዊው ስርዓት ላይ የከረረና የማይለዝብ ተቃውሞ ነበራቸው። ተማሪዎች፤ በተለይ ወደ መጨረሻው የንጉሱ ዘመን፤ የብሄር ብሄረሰቦችን ጥያቄ ከመሬት ላራሹ ባላነሰ ሁኔታ አቀንቅነውታል (ባህሩ ፣1983፣231-236)። የብሄር ጭቆና አቀንቃኝ ኃይሎች የአማራ ህዝብ እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ህዝብ ተጨቋኝ ሆኖ ሳለ በሆያ ሆየ በጨቋኝነት ፈርጀውታል። ይህ የሆያ ሆየ ፍረጃ የአማራን ህዝብ የኋላ የኋላ ሥርዓታዊና መዋቅራዊ ለሆኑ ጥቃቶች ሰለባ አድርጎታል። የዚህ አደገኛ ፍረጃ መነሻዎች ለመረዳት ይረዳን ዘንድ በቅድሚያ ስለ ብሄር ጭቆና ያሉትን እውነታዎች መመርመር ጠቃሚ ነው።

በድህረ ጣሊያን ስለ ኢትዮጵያና ህዝቦቿ ግንኙነት ሁለት እይተዋች ነበሩ። አንዱ የኢትዮጵያን ብዙሃዊነት፤ ውበትና አንድነት/አብሮነት የሚገልፅ ሲሆን ሁለተኛው ግን ከአብሮነት ይልቅ ልዩነትን የሚያጎላ ነው። የመጀመሪያውና በብዝሃነት ውስጥ አብሮነትን የሚያጎላው እይታ Ethiopia is the “Museum of People” (ኢትዮጵያ የህዝቦች ህብር ናት) የሚለው ነው (Teshome ፣ 1980/81፣69)። ልዩነታቸው እንዳለ ሆኖ እነዚህ ብሄረሰቦች / ማህበረሰቦች የሚጋሩት ዘርም ሆነ ባህል የሌላቸውና ፍፁም በማያቀላቅል ድንበር ተከልለው በተናጠል የሚኖሩ፤ የማይለወጡ ሳይሆኑ፤ በታሪክ ሂደት በስደት፤ በጦርነት፤

በንግድ፤ የጋራ እምነት በመያዝና መንፈሳዊ ጉዞ በማድረግ፤ በጋብቻና አንዱ ያለውን ለሌላው በማቅረብና በመቀበል ወዘተ. የተቀላቀሉና የተሳሰሩ እንደሆኑ ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡ ምንም እንኳ አስተማማኝ ማስረጃ ባይኖርም እኤአ በ1992 ዓ.ም ቅይጥ ማንነት ያላቸው ከ20-40% የህዝብ ቁጥር እንደሚይዙ ይገመታል (Levine ፣ 2012፣35)፡፡

ሁለተኛውና ወደ መጨረሻው የንጉሱ ዘመን ጎልቶ የወጣው እይታ “Ethiopia is a Prison House of Nationalities” ( Levine ፣ 2012፣35) (ኢትዮጵያ የብሄር ብሄረሰቦች እስር ቤት ናት) የሚለው ነው፡፡ ይህ እይታ ኢትዮጵያዊያን የሚጋሩት ዘርም ሆነ ባህል የሌላቸው የተለያዩ ማህበረሰቦች ስብስብ አድርጎ ከመገንዘብ ይመነጫል፡፡ ለዚህ ጥሩ ማስረጃ የዋለልኝ ፅሁፍ ነው፡፡ እንደ ዋለልኝ ገለፃ ኢትዮጵያ ሃገረ-ብሄር ሳትሆን የራሳቸው ቋንቋ፤ የአለባበስ ዘይቤ፤ ታሪክ፤ ማህበራዊ አደረጃጀትና ግዛት ያላቸው የደርዘን ብሄሮች ስብስብ ናት (Bahru፣ 2014፣ 200፤Tesfaye፣ 2005-2006፣ 58)፡፡ በዚህ እይታ ሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች ከአማራ በስተቀር በፖለቲካ እኩል ሲሆኑ ነገር ግን ሁሉም በአማራ ወይም በአማራና ትግሬ ጭቆና ስር ናቸው፡፡ ይህ በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ለረጅም ጊዜ የቆየ ዕውነት እንደሆነ ተገመተ፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት ስለ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች ምን እንደሚሰማቸው አለመጠናቱ ነው፡፡ ለዘርፉ ቀረቤታ ያላቸው የስነ ዝርያ/ethnographer) ምሁራን እኤአ በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ በአያሌ የብሄር ቡድኖች ላይ ባጠኑት ጥናት ግን አንዳቸውም በብሄር እስር ቤት የአኗኗር ስሜት ውስጥ መኖራቸው አልተጠቀሰም (Levine፣2012፣35)፡፡ በተጨማሪም የብሄር ጭቆና የድህረ ነፃነት ኢትዮጵያ የታሪክ ሁነት አለመሆኑን ሰፋ ባለ መልኩ ለመረዳት ያስችለን ዘንድ ሶስት ጠቋሚዎችን ማለትም የፖለቲካ ውክልናን፤ የዘመናዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አውታሮች ተደራሺነትንና የባህል መስተጋብርን ከዚህ እንደሚከተለው እንዳስሳለን፡፡

ተዛማጅ ጥናቶች የሚያሳዩት የንጉሳዊ ቤተሰብ ኀብረ-ብሄራዊ ማንነት ያለው መሆኑን ብቻ ሳይሆን (Maimire Mennasemay፣ 2005-2006፣9) የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግስት የአማራ ልሂቅ የበላይነት ቢታይበትም ፍፁም አግላይ አለመሆኑን ጭምር ነው፡፡ በመሆኑም በፖለቲካል ጋብቻና በሹመት አያሌ ትግሬና ኦሮሞ የሃገረ-መንግስቱ ልሂቅ አባል ነበሩ (Levine፣2012፣36)፡፡ እነዚህ የሃገረ-መንግስቱ ልሂቅ አባላት የወጡበትን ብሄር ጨቋኝና በዝባዥ እንደነበሩ የፖለቲካ

ምሁራን ይሞግታሉ (Tesfaye፣2005-2006፣59)፡፡ ይህም በወቅቱ የነበረው ጭቆና የብሄር ሳይሆን የመደብ መሆኑን ማሳያ ነው፡፡ሌላው የመደብ ጭቆና ማሳያ የገበሬዎች አመፅ ነው፡፡ የገበሬዎች አመፅ የተከሰቱት የጎሳ የጎሳ የብሄር ጭቆና ባቀነቀኑት ማህበረሰቦች ብቻ ሳይሆን የገዢው መደብ ማህበራው መሰረት ነው ተብሎ በሚታሰበው የአማራ ህዝብ ጭምር ነው፡፡ ለዚህም የጎጃምና የየጁ ገበሬዎች አመፅ ጥሩ ማሳያዎች ናቸው (ባህሩ፣1983፣226-229)፡፡

በድህረ-ነፃነት ኢትዮጵያ ዘመናዊ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አውታሮች ተስፋፍተዋል፡፡ በዘርፉ የተሰሩ የምርምር ግኝቶች እንደሚጠቁሙት ከሆነ ዘመናዊ የኢኮኖሚና ማህበራዊ አውታሮች (ፋብሪካዎች ፣ የትምህርት ተቋማት፣የጤና ተቋማት፣የባቡር ትራንስፖርት እና የመሳሰሉት) በጨቋኝነት ከተፈረጀው የአማራ ህዝብ ይልቅ በጭቆና ስር ነን ለሚሉት ብሄረሰቦች ተደራሽ ነበሩ (ባህሩ ፣ 1983 ፣ 206-208)፡፡ ለምሳሌ ያህል የትምህርት ተቋማት በጥሩ ሁኔታ ተደራሽ የነበሩት አዲስ አበባ፣ ሸዋና ኤርትራ (Bahru፣2014፣44) ሲሆን ፋብሪካዎች፣ የባቡር ትራንስፖርትና የመሳሰሉት ደግሞ አስመራና በመሃል አገር ደግሞ በአዲስ አበባና በድሬ ደዋ መካከል ነበር(ባህሩ፣ 1983፣ 206-208)፡፡ እነዚህ አካባቢዎች በግምት 80 ፐርሰንት የሚሆነው የአማራ ህዝብ መገኛ ከሆኑት ጎጃም ጎንደርና ወሎ በጣም የራቁ ናቸው፡፡ ይህ እውነታ የሚያሳየን የአማራ ህዝብ በስርዓቱ የተለየ ተጠቃሚ መሆኑን ሳይሆን እንዲያውም በጣም ተጎጂ ከነበሩት የሚመደብ መሆኑን ነው፡፡ በጥቅሉ የምርምር ስራዎች የሚያሳዩት በኢትዮጵያ የዘመናዊ የኢኮኖሚና ማህበራዊ አውታሮች ለምሳሌ የትምህርት ተቋማት የጎላ የተደራሺነት ልዩነት የነበረው በማንነት መካከል ሳይሆን ከጠቅላይ ግዛት ጠቅላይ ግዛትና እንዲሁም በከተማና በገጠር መካከል ነው (Balsvik፣1985፣6-7)፡፡

ኢትዮጵያዊያን በአንድም ሆነ በሌላ የተሳሰሩና የተቀላቀሉ ስለሆነ የባህል መወራረስ የግድ ነው፡፡ ይህም አንድ የሱ ወይም የኔ ተብሎ በብቸኝነት የሚሰጥ/የሚያዝ ቱባ ባህል እንዳይኖር ያደርገዋል፡፡ የድህረ ነፃነት ኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ደግሞ አገር በቀል የሆነን ባህል የሚያበረታታ አልነበረም፡፡ ከፅንሰ-ሃሳቡ እንደምንረዳው ዘመናዊነት በስልጣኔ የቀደሙ የምዕራባዊያንን ፈር መከተል ነው፡፡ በመቋቋም አቅማቸው የሚለያዩ ካልሆነ በስተቀር ሁሉም የኢትዮጵያ ባህሎች የአማራን ጨምሮ ለዘመናዊነት ተፅዕኖ ተጋላጭ ነበሩ፡፡ ዘመኑ የውጭ

ባህል በወጣቱ ትውልድ እጅግ በጣም እየሰረፀ የመጣበት ነበር፡፡ ይህንንም ተከትሎ የወግ አጥባቂውና የተማሪው አክራሪ ክንፍ ተቃውሞ አሰምተው ነበር (Eyayu፣1994፣29)፡፡ እኤአ በ1968 የተማሪዎች ንቅናቄ ተቃውሞ ያሰማበት የፋሺን ትዕይንት /fashion show /(Legesse፣1979፣38) የዚህ ተቃውሞ አንዱ ክፍል ነው፡፡ በወቅቱ የሚዜሙት "ለእኛ ማይስማማ ግንጥል ጌጥ ምንድን ነው፤ ባህላችን ይበቃል ሌላ የሌላ ነው"(Eyayu ፣1994፣30) የሚለውና ሌሎች ተመሳሳይ መዝሙሮች የሚያሳዩን የችግሩን ጥልቀት ነው፡፡ የሥርዓቱ ቁንጮ የሆነው የመንግስት አካልም ዘመናዊነትን የሚያወድስ ተራማጅ እንጂ ባህሉን የሚጠብቅ ልማዳዊ አልነበረም (Levine ፣ 1961፣11)፡፡ ስለሆነም ልማዳዊ የሆነውን የኔ የሚለውን ቱባ ባህል የሚጠብቅና በሌሎች ላይ የሚጭን አልነበረም፡፡ የአማራ ባህል በላቀ ተፈጥሯዊ ዕድገቱ የሌሎችን ባህል መጫን ችሎ ካልሆነ በስተቀር መንግስታዊ ድጋፍ የሌለው መሆኑን ይህ ጥሩ ማሳያ ነው፡፡ በተፈጥሯዊ ዕድገቱ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ደግሞ በፖለቲካ ሊፈታ የሚችል ጉዳይ አይደለም፡፡

የባህል ጭቆና ሲነሳ ደግሞ ጎልቶ የሚወጣው የቋንቋ የበላይነት ነው፡፡ በንጉሱ ዘመን አማርኛ ብሄራዊ ቋንቋ ስለሆነ ብቸኛ የትምህርትና የስራ ቋንቋ መሆኑ ለባህል ጭቆና እንደምክንያት ይጠቀሳል፡፡ በመሰረቱ አማርኛ በህግ አግባብ የሀገሪቱ ብሄራዊ ቋንቋ የተደረገው እኤአ በ1955 ተከልሶ በተዘጋጀው ህገ-መንግስት ነው፡፡ የአንደኛ ደረጃ የትምህርት ቋንቋ የሆነው ደግሞ እኤአ ከ1963 ጀምሮ ነው(Bahru፣2008፣85-87)፡፡ ከዚህ በፊት የኃይማኖትም ሆነ ዘመናዊ ትምህርትን በአፍ መፍቻ ቋንቋው እየሰጠ ቆይቶ በአማርኛ እንዲያስተምር የተገደደ ብሄር፤ ብሄረሰብና ህዝብ በኢትዮጵያ ስለመኖሩ የሚጠቅስ መረጃ የለም፡፡ ዘመናዊ ትምህርት ወደ አገራችን ከገባ ጊዜ ጀምሮ ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ የትምህርት ቋንቋ እንግሊዝኛና ፈረንሳይኛ ነበሩ፡፡ ለግማሽ ክፍለ ዘመን ያክል ትምህርትን በአማርኛ ቋንቋ መስጠት ያልተቻለው በሰው ሃይልና በፋይናንስ ችግር ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡ የዳበረ ስነ-ፅሁፍና የተማረ የሰው ሃይል ያለውን አማርኛ የትምህርት ቋንቋ ለማድረግ ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ ከወሰደ፤80 የአፍ መፍቻ ቋንቋዎችን በአንድ ጊዜ የትምህርት ቋንቋ ማድረግ የማይታሰብ ሆኖ ሳለ አማርኛ የትምህርት ቋንቋ መሆኑ ለጭቆና መሳሪያ ታስቦ እንደነበር አድርጎ መሳሉ ምክንያታዊ አይደለም፡፡

አማርኛ ሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች የሚናገሩት ብሄራዊ ቋንቋ ከመሆኑና ትምህርትን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ለማዳረስ አስቻይ የሰው ኃይል፤ ቁሳቁስና ፋይናንስ አቅም ካለመኖሩ የተነሳ ብቸኛ የትምህርት ቋንቋ መሆኑ አማራጭ የሌለው ነው። የስራ ቋንቋም ትልቅ የሰው ኃይል፤ ቁሳቁስና ፋይናንስ የሚጠይቅ ስለሆነ በኢትዮጵያ በዘመኑ የእድገት ደረጃ ብዙ ቋንቋዎችን ለማሳተፍ የሚቻል አልነበረም። ከዚህ በተጨማሪም ኢትዮጵያ ካሏት ብዙ ቋንቋ ተናጋሪዎች አንፃር የግድ አንድ የጋራ /ብሄራዊ/ ቋንቋ መምረጥ ስለሚያስፈልግ አማርኛ ሁሉም ብሄሮች የሚግባቡበት፤ የፊደልና የዳበረ ሥነ-ፅሁፍ ባልተቤት ብሎም በጣም ያደገ ቋንቋ (Bahru፤2008፣85-87)በመሆኑ በሁሉም ዘርፍ ተመራጭ ያደርገዋል። አማርኛን ቋንቋ በጨቋኝነት የሚወነጂሉና ቋንቋቸው አገራዊ የትምህርትና የስራ ቋንቋ እንዲሆንላቸው ከሚፈልጉ ዋነኞቹ ከብሄራቸው ውጭ ተናጋሪ የሌለው የቋንቋ ባለቤቶች ናቸው። የነዚህ ቡድኖች ጥያቄ ከራስ ወዳድነት የመነጨ እንጂ ብዙሃኑን ኢትዮጵያዊያንን እንዴት ማካተት ይቻላል የሚለውን የእኩልነት ጉዳይ አያስተናግድም። ብሄራዊ ቋንቋ የሚሆንና በሁለንተናዊ መልኩ ተወዳዳሪ ሆኖ አማርኛን የሚተካ አማራጭ ቋንቋ ሲያቀርቡም አይታዩም።

ይህ ከሆነ የብሄር ጥያቄ እንዴት ሊነሳ ቻለ ብለን ስንጠይቅ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የህዝቡን ቅሬታና ብሶት፤ ምንጩ ምንም ይሁን ምን፤ ተቀብለው ርዕዮት-ዓለማዊ ቅርፅ እንዲይዝ አደረጉት እንጂ፤ የብሄር ጥያቄ በተማሪዎችም ወይም በዩኒቨርሲቲ ውስጥ አልተጀመረም የሚሉ የምርምር ስራዎችን እናገኛለን (Teshome፣1980/81፣74)። ይህ ሃሳብ የሚነግረን ተማሪዎች የህዝብን ቅሬታና ብሶት በወቅቱ ከነበረው የሶሻሊስት ርዕዮት እይታ አንፃር ማቀንቀናቸውን ነው። በእርግጥ ስለ ኢትዮጵያ ችግር ከመደብ ጭቆና (Class Oppression) እና ከብሄር ጭቆና (Ethnic Oppression) አንፃር የተሰጡ ትንታኔዎች ሁሉ መነሻቸው የሶሻሊስት ርዕዮት-ዓለም ንድፈ-ሃሳብ ነው። ይሁን እንጂ ተማሪዎች የብሄር ጭቆናን በምርምር የደረሱበትና ያረጋገጡት የታሪክ ዕውነታ ካልሆነና፤ ከህዝብ የተቀበሉት ያልተፈተሸ ሃሳብ ከሆነ፤ ከህብረተሰቡ ውስጥ ልዩ ፍላጎት ካላቸው ቡድኖች የመነጨና መሬት ላይ የሌለ ችግር ሊሆን ይችላል። ይህም ዋለልኝ መኮንን በተለያዩ አጋጣሚዎች ከሌሎች ብሄር ተወላጆች ጋር የነበረው የቀረበ ግንኙነት በፖለቲካ እሳቤው ላይ ተፅዕኖ አሳድሮበታል የሚሉ ግለሰቦችን ሃሳብ ያጠናክርልናል (Abdul ፤2010፣99)። በእርግጥም ዋለልኝ የመጀመሪያ ድግሪ

ተማሪ በመሆኑ እንድህ ያለውን ሰፊና ጥልቅ ምርምር የሚጠይቅ ጉዳይ ለማጥናት የሚያስችል ጊዜ፣ ገንዘብ፣ ክህሎትና ዕውቀት ሊኖረው አይችልም። ስለዚህ የዋለልኝን ፅሁፍ የመወያያ ርዕስ ያደረገው የምርምሩ ብቃት ሳይሆን ልዩ ፍላጎት ያለው ቡድን እንደነበር ብንገምት ስህተት አንሆንም። በአጠቃቃላይ ከላይ ከተሰጡት ገለፃዎች የምንረዳው የብሄር ጭቆና የኢትዮጵያ የወቅቱ ችግር ነው ብለው የሚያቀነቅኑ ተማሪዎቸና ልሂቃን በቂ የምርምር ክህሎትና ዕውቀት የሌላቸውና መረጃቸውም ጠንካራ ያልሆነ መሆኑን ነው። በዚህም ይሆናል የብሄር ጭቆና ስለመኖሩ እስከአሁን ድረስ ስምምነት ላይ አልተደረሰም። ይሁንና ተማሪዎች የብሄር ጭቆናን ያቀነቀኑበት አግባብ በኢትዮጵያ ያሉ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች የተበድለናል ስሜት እንዲያዳብሩና በጥላቻ መንፈስ በአማራ ህዝብ ላይ ለበቀል እንዲነሳሱ እንዳደረገ የጎላ የጎላ ታሪካዊ ሁነቶች ያስረዳሉ።

በጥቅሉ በመደብ ጭቆና አመክንዮ ተቃውሞ ያነሳው ሃይል ምሁራኑን ፣ ወታደሩን ፣ ተማሪውንና እንዲሁም የገዢው መደብ አባላትን ያካትታል። ተቃውሟቸውም ኢላማ ያደረገው የመንግስት ለውጥን ነው። ለዚህም ይመስላል የመንግስት አፀፋም ከባድና እስከ ስቅላት የደረሰ ነበር። ፍጥጫው በሁለቱም በኩል ከባድ ኪሳራን አስከትሏል። ከዚህ በፊት እንደተጠቀሰው የዚህ ኃይል ማህበራዊ መሰረቱ በአብዛኛው አማራ ነው። በመሆኑም በግጭቱ ከደረሰው ከፍተኛ ሰብአዊም ሆነ ቁሳዊ ጉዳትና ተያይዞ ከመጣው የኃይል መከፋፈልና መዳከም ሰለባ የሆነው የአማራ ህዝብ ነው። በአንፃሩ የብሄር ጭቆና አቀንቃኙ ቡድን እየተጠናከረ መምጣቱን ታሪካዊ ሁነቶች ያሳያሉ። እንደሚታወቀው በብሄር ጭቆና ስሜት የተሰበቀው ተቃውሞ አነሳሱ በገበሬዎች አመፅ ሆኖ ቀስ በቀስ የተማሪውን ድጋፍ አግኝቷል። የመደብ ጭቆናን አንግቦ ፀረ-ፊውዳልና ፀረ-ካፒታሊስት ተቃውሞ ይሰብቅ የነበረው ተማሪ የጎላ የጎላ የብሄር ጭቆናን ሲያቀነቅን ታይቷል። ወደ መጨረሻው የንጉሱ ዘመን የተማሪዎች ንቅናቄ ከመደብ ጭቆና ይልቅ ለብሄር ጭቆና ትኩረት በመስጠት ይመስላል“Ethiopia is a Prison House of Nationalities”(Levine፣ 2012፣35) (ኢትዮጵያ የብሄር ብሄረሰቦች እስር ቤት ናት) የሚለውን ሃሳብ ያቀነቅኑ ነበር። የብሄር ጭቆና አቀንቃኙ ኃይል መጠናከር ዋና ማሳያው ግን አደረጃጀቱ ከህቡዕ ወደ ግንባር መሸጋገሩ ነው። የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት የተደራጀው የሜጫ ቱለማ መረዳጃ ማህበር የኦሮሞ ነፃ አውጪ

ግንባርን ወልዷል፡፡ በተመሳሳይ ቀደም ብለው የተመሰረቱት የትግራይ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማህበር (Tigray University Student Association) እና ሌሎች ህቡዕ አደረጃጀቶች በአብዮቱ ዋዜማ ላይ ህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይን ፀንሰው በአብዮቱ ማግስት ወልደውታል (Bennett ፣ 1983 ፣ 96 ፣ Bahru, 2014፣258-262)፡፡ እነዚህ ህቡዕ አደረጃጀቶችም ሆኑ የብሄር ግንባሮች እንዲመሰረቱና እንዲጠናከሩ ደግሞ በተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ ተሳታፊ የነበሩ የኦሮሞና የትግራይ ተማሪዎች ከዚህም ከዚያም አበክረው ይሰሩ እንደነበር ጥናቶች ያስረዳሉ (Asafa፣1995፣173)፡፡ በአንፃሩ በጨቋኝነት ከተፈረጀው የአማራ ህዝብ አብራክ የወጣው ተማሪ ከብሄር እሳቤ ውጭ የጭቁኖችን ችግር ሲያሰተጋባ መቆየቱ ወካይና ጥሩ ሆኖ ሳለ ባልተረጋገጠ መረጃ የብሄር ጭቆናን አቀንቅኖ ወይም በግዴለሺነት[2]፤ ከዚያም ተተኪ በሌለበት ንጉሳዊ አገዛዙን ለማፍረስ ተግቶ መስራቱ፤ በወቅቱ በሃገሪቱ ውሥጥ እየሆነ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በደንብ ያላገናዘበ ጉዞ መሆኑን በግልፅ ያሳየናል፡፡ የአማራው ኃይል የብሄሮችን ጭቆና እያቀነቀነ ተባባሪ ሆኖ ሳለ አጋርነቱን ወደ ጎን ትተው በብሄር እየተደራጁ የነበሩ ቡድኖች ፍላጎትና ዓላማ ምን እንደሆነ ለመረዳት አልሞከረም፡፡ በማንነት ስሜት የተሰበቁ ትግሎች ኢላማ ያደረጉት አማራን ነው፡፡ የብሄር ጭቆና አቀንቃኙ ኃይል በማንነታቸው "ለተጨቆኑ" ማህበረሰቦች መብት ሲታገል፤ በማንነታቸው ለተጠቁት አማራዎች፤ የጥቃቱ መጠን ከፍተኛም ይሁን ዝቅተኛ፤ ምንም ያለው ነገር የለም፡፡ብሄርተኛው እየተደራጀ ሲመጣ የጥቃቱ መጠን እየሰፋ ሊመጣ እንደሚችል የአማራው ኃይል የተገነዘበ አይመስልም፡፡ ይህ የሚያስረዳን የአማራው የብሄር ንቃተ-ህሊና ማደግ ቀርቶ መፈጠር አለመቻሉን ነው፡፡ እንደ ኦሮሞና ትግሬ የአማራ ብሄርተኝነት ቢወለድ ኖሮ ተገዳዳሪ አደረጃጀት በመፍጠር የሃይል ሚዛን ማስጠበቅ ስለሚችል ብሄርተኞቹን አንድም ወደ ህብረ-ብሄራዊ ፖለቲካ እንዲመጡ ጫና ማድረግ ካልሆነ ደግሞ እሾክን በሾክ እንዲሉ በተመሳሳይ አደረጃጀት ጥቃቱን መግታት ይችል ነበር፡፡ የንጉሱ ስርዓት ከፈረሰ በኋላ ብሄርተኛው ቡድን በጨቋኝነት በፈረጀው የአማራ ህዝብ ላይ በጥላቻና በበቀል ስሜት ወደ ጥቃት ሊጓዝ እንደሚችል ሰፋ አድርጎ በማሰብ ከነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚመጥን የሃይል አሰላለፍ ማድረግ ሲገባው፤ የብሄር ጥያቄ ጎልቶ ከመውጣቱ በፊት ጀምሮ በውስጥ ሸኩቻ ራሱን አዳክሟል፡፡ ኦነግና መሰል

[2] የብሄር ጭቆናን የማያቀነቅነው የአማራ ኃይልም ቢሆን የብሄርተኞችን እንቅስቃሴ እያየ ግልፅ ተቃዋሚ ኃይል ሆኖ አስመውጣቱ በተባባሪነት ያስወቅሰዋል፡፡

ህቡዕ የትግሬ ድርጂቶች በተፈጠሩበት ወቅት ሌላው ቀርቶ ህብረ-ብሄራዊ ፓርቲ አልመሰረተም፡፡ በጥቅሉ አማራ ጨቋኝ መሆኑን የሚሰብኩ ፅሁፎች በሰላ የምሁራን ትችት ሳይፈጩ ለህትመትና ለመወያያ ሰነድ መብቃታቸው ፤ በጥናት ያልተረጋገጡ ታሪካዊ ሁነቶች ለብሄርተኛው ቡድን መቀስቀሻ ሲውሉ በህግም ሆነ በኃይል አለመገታታቸው፤ ብሄርተኛው ቡድን ሲበራከት፤ ሲደራጅና ሲደረጅ፤ ተገዳዳሪ የአማራ የፖለቲካም ሆነ ወታደራዊ ሃይል አለመፈጠሩ የኋላ ኋላ በአማራ ህዝብ ላይ ለተፈፀሙ ሁለንተናዊ ጥቃቶች መነሻዎች ናቸው፡፡

**የወታደራዊው አስተዳደር ዘመን**

የኃይለ ሥላሴ መንግስት ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች የተነሱ ተቃውሞዎችን አስተናግዷል (ባህሩ ፣ 2011 ፣ 38 ፣ 40)፡፡ ይሁንና በስተመጨረሻ የዘውዱን ስርዓት ያፈረሰው ከወታደሩ ልዩ ልዩ ክፍሎች ተውጣጥቶ የተቋቋመው ኮሚቴ ወይም ደርግ ነው፡፡ ደርግ በአጭር ጊዜ ስልጣን ለመያዝ ይረዳው ዘንድ ወደ ስልጣን ማማተር በጀመረበት ጊዜ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናትን፤ የጦር መኮንኖችን፤ መሳፍንቱንና ከነሱ ጋር ግንኙነት ይኖራቸዋል ብሎ የሚያስባቸውን ሁሉ በቁጥጥር ስር አዋለ፡፡ ከዚያም እኤአ ሴፕቴምበር 1974 ንጉሱን በማስወገድ ስልጣን ተቆጣጠረ፤ ራሱንም "የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ" ብሎ ሰየመ (ባህሩ ፣ 1983፣244-247)፡፡ ከሶስት ወር በኂላ ቀደም ብሎ ያሰራቸውንና በተለምዶ 60 የቀድሞው መንግስት ባለስልጣኖች በመባል የሚታወቁትን መሳፍንት ፤ የቤተ-መንግስት ባለሟሎች፤ ሚኒስተሮች ፤ የጦር አዛዦችና የጠቅላይ ግዛት እንደራሴዎችን በአንድ ቀን ረሸነ (Ottaway ፣ 1977 ፣ 85)፡፡ በተጨማሪም የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግን መመስረት የተቃወሙና ከሁሉ በፊት "ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት" ከዚያም "ህዝባዊ መንግስት" እንዲመሰረት አማራጭ ያቀረቡ የሲቪልና ወታደራዊ ክፍሎችን እና የግራ ክንፍ ፖለቲካ ፓርቲዎችን እንቅስቃሴ የተቆጣጠረው በግድያና እስራት ነበር (ባህሩ ፣ 1983 ፣ 247-248፣255)፡፡

በኢትዮጵያ ብሄርተኛም ሆነ ኅብረ-ብሄራዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች ብቅ ብቅ ማለት የጀመሩት በንጉሱ የመጨረሻዎቹና በደርግ የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ነው፡፡ ለዚህም የተማሪዎች ንቅናቄ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል፡፡ የአብዛኞቹ ብሄርተኛም ሆኑ ኅብረ-ብሄራዊ ፓርቲዎች አነሳስ በአንድም ሆነ በሌላ ከተማሪዎች ንቅናቄ ይመዘዛል፡፡ ኢህአፓና መኢሶን ቀጥተኛ ተወላጅ ቢሆኑም የትህነግ፤ ኦነግ እና ኢህዴን

አፈጣጠርም ከዚሁ ንቅናቄ ይያያዛል፡፡ የኤርትራ ነፃ አውጪ ግንባር በርዕዮተ-ዓለምና አደረጃጀቱ ከተማሪዎች ንቅናቄና የኋላ የኋላ ከተማሪዎች ንቅናቄ የበቀሉ የግራ ክንፍ ፓርቲዎች ጋር ቀጣይ በሆነ ግንኙነት ያደገ ግንባር ነው (Bahru፣ 2010 ፣ 2 ፤ Joireman፣1997፣389)፡፡ ከነዚህ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ግንባሮች አመሰራረት የምንረዳው፤ የተማሪዎች ንቅናቄ የሚስማሙም ሆነ የማይስማሙ ብዙ ፍላጎቶችን ያነገቡ ኃይሎች ስብስብ መሆኑን ነው፡፡

ፍላጎታቸው የተለያየ ቢሆንም አብዛኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ሁሉም ነፃ አውጪ ግንባሮች የደርግን ወደ ስልጣን መምጣት በበጎ አላዩትም፡፡ "የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት" መመስረትን እንደ አማራጭ ይዘው ከመጡት የግራ ክንፍ ፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል በዋናነት ኢህአፓንና መኢሶንን እናገኛለን፡፡ ይሁንና መኢሶን እኤአ ከ1975 ጀምሮ ሃሳቡን መቀየር ብቻ ሳይሆን ጠንካራ የኢህአፓ ተቃዋሚ ሆኖ ቀረበ፡፡ ሌሎች እንዳሉ ሆኖ ዋናው ምክንያት መኢሶን እንደ ኢህአፓ በመምህራን፤ ተማሪዎችና ሰራተኞች ማህበራት ሰርጎ ስላልገባ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስቱ የመመስረት ዕድል ቢኖረው ስልጣን በቀላሉ መቆጣጠር እንደማይችል ስለተገነዘበና ከዚህ ደረጃ አስከሚደርስ ከደርግ መወገኑን ስለመረጠ ነበር (ባህሩ ፣ 1983 ፣ 256)፡፡ ርዕዮተ-ዓለምና ፓርቲ ለሌለው ደርግ (Keller ፣ 1985 ፣ 3) መኢሶንንና ሌሎች የግራ ክንፍ ፓርቲዎችን በአጋርነት መያዙ (ለምሳሌ ወዝሊግ) ከማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተ-ዓለም ጋር እንዲተዋወቅ ምቹ ሁኔታን ፈጠረለት፡፡ በመቀጠልም እኤአ በ1976 የራሱን ፓርቲ አብዮት ሰደድ /Revolutionary Flame/ን መሰረተ(ባህሩ፣ 1983፣256)፡፡ ቀስ በቀስ ከሶሻሊስት ርዕዮተ-ዓለም ጋር እየተዋወቀ ሲመጣ፤ ማን ከማን ያንሳል የሚል ስሜት አዳበረ (Chege፣1979፣378)፡፡ ከመኢሶንና ሌሎች የግራ ክንፍ ፓርቲዎች ጋር የመሰረተውን አጋርነት በብልሃት በመያዝ ሙሉ ኃይሉን "Trotskyites" and "anarchists" ብሎ ከፈረጀው ኢህአፓ ላይ አደረገ፡፡ ለዚህም ይረዳው ዘንድ የግለሰቦችን ትጥቅ አስፈታ፡፡ ለምሳሌ ከቀይ ሺብር ዘመቻ ቀደም ብሎ ከአዲስ አበባና ጎንደር ከተማዎች እንደቅደም ተከተላቸው ሰባ ሺ እና ሰባት ሺ አውቶማቲክና የቃታ መሳሪያዎች ሰበሰበ (አስናቀ፣መጋቢት 1994 ዓ.ም፤ 200)፡፡ ከዚያም በቀይ ሺብር ዘመቻ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶችን ጨፈጨፈ፡፡አያሌዎችን ደግሞ ወደ ከርቸሌ አጋዘ፡፡ ቀጥሎም ቀደም ሲል መኢሶንን "Opportunist"፤ ወዝ ሊግን "Maoists"፤ ኢጭአትን "narrow nationalists" ብሎ

በፈረጃቸው መሰረት አንድ በአንድ አጠፋቸው፡፡ እኤአ በ1979 ዓ.ም መጀመሪያዎቹ ወራቶች ላይ የደርጉ ሰደድ ብቸኛውና ህጋዊ የፖለቲካ ፓርቲ ለመሆን በቃ (Keller ፣ 1985 ፣ 9)፡፡ ይህ ጫካ ለገባው ብሄርተኛ ቡድን መልካም አጋጣሚ ነበር፡፡ ምክንያቱም ብሄርተኛው ቡድን አቅሙን የማጠናከሪያ ጊዜ ከማግኘቱ በተጨማሪ የሁለቱ ፍጥጫ በአንድ በኩል የአንድነቱን ኃይል አዳክሞለታል በሌላ በኩል ደግሞ የቀይ ሺብር ጭፍጨፋ ደርግን ከህዝብ ነጥሎታል፡፡

በአብዮቱና በአብዮቱ ማግስት የአማራ ህዝብ ከአንድም ሁለት ትውልድ አጥቷል፡፡ ይህም የአማራ አባትና ልጅ የጠፉበት ዘመን ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ እንደሚታወቀው አብዮቱ የበላቸው መሳፍንትና መኳንንት የአማራ አባቶች ናቸው፡፡ የቀይ ሺብር ሰለባዎች ደግሞ የአማራ ወጣት ወንድምና እህቶች ናቸው፡፡ ይህም የሆነው ቀደም ሲል እንደተገለፀው ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የተማሪዎች ንቅናቄ ተሳታፊዎች የአማራ ተማሪዎች በመሆናቸውና ከነዚህም ውስጥ የኦሮሞ ተማሪዎች ኦነግን፤ የትግራይ ተማሪዎች ህውሃትን፤ የኤርትራ ተማሪዎች የኤርትራ ነፃ አውጪ ግንባርን ተቀላቅለው በረሃ ሲወርዱና (Markakis ፣ 1989 ፣ 123፤ Bahru፣2014፣258-262)የደቡብ ኢትዮጵያ ተማሪዎች (በተለይ ኦሮሞዎች በብዛት የተሳተፉበት) ደግሞ የደቡብ ኢትዮጵያን ህዝቦች እወክላለሁ ብሎ የተነሳው የኢትዮጵያ ጭቁኖች አንድነት ትግል (የኢጭአት)ን (ባህሩ ፣ 1983 ፣ 256 ፤ Bahru ፣ 2014 ፣ 258-262) ሲቀላቀሉ፤ በኢህአፓ ውስጥ የቀረው ኃይል ሙሉ በሙሉ በሚባል መልኩ የአማራ ልሂቅና ተማሪ በመሆኑ ነው፡፡ ለዚህም ይሆናል አንዳንድ ፀሃፊዎች ኢህአፓ የአማራው ፓርቲ ተብሎ እንደሚጠራ ይጠቅሳሉ (Chege፣1979፣372-377፤ Vaughan ፣2003 ፣ 147)፡፡ ይህ የሚያስረዳን በቀይ ሺብር ጭፍጨፋና የስነ-ልቦና ስብራት ከማንም በላይ ተጎጂ የሆነው የአማራ ህዝብ መሆኑን ነው፡፡ ለምሳሌ ያክል በጎንደር ክፍለ ሃገር በወቅቱ በነበረው የደርግ ባለሟል የተካሄደውን የቀይ ሺብር ጭፍጨፋ የአማራ እናት እንድህ ገልፃዋለች፡፡

መላኩ ተፈራ የእግዜር ታናሺ ወንድም፤ የዛሬን ማርልኝ ከእንግድህ አልወልድም፡፡[3]

ከሁለቱ ታሪካዊ ክስተቶች የተረፉት የአማራ አባትና ልጆች የሳት እራት የሆኑበት ደግሞ የሶማሌ ወረራ፤ የራዛና ቀይ ኮከብ ዘመቻዎች ናቸው፡፡ ደርግ የገጠመውን የሶማሌ ወረራ እና የኤርትራ ተገንጣዮች የመስፋፋት አደጋ ለመቀልበስ እኤአ በ1976 አጋማሽ ላይ ላስተላለፈው

[3] የህዝብ ግጥም፡፡

የክተት ጥሪ በአገር ነፃነትና አንድነት የማይደራደረው የአማራ ህዝብ የተመመው ከሊቅ እስከ ደቂቅ ነበር፡፡ መንግስት አጭር ስልጠና ሰጥቶ ካሰለፈው ሚሊሻ (Gebru፣2000፣642) በተጨማሪ ቀደም ሲል በባላባት ስም ሲታደን የነበረው ነፍጠኛ አማራ መጀመሪያ የራዛ ቀጥሎ የቀይ ኮከብ ዘመቻን ጥሪ ተቀብሎ ዕድሜና ጤናው የፈቀደለት በአካል፤ አቅሙ የደከመና ጤናው የታወከ ደግሞ ልጁን ወይም የቅርብ ዘመዱን መሳሪያውን አስታጥቆ ልኳል፡፡ የመንግስትን ጥሪ ተቀብሎ ከወሎ ክፍለ ሃገር ብቻ በራዛ ዘመቻ የተሳተፈው 10ሺ የአማራ ገበሬ የገጠመው የዘመናዊ ሥልጠና ካለው የጠላት ሰራዊት ጋር ነበር (ባህሩ፣1983፣270)፡፡ ይህም ለከፍተኛ ጉዳት ዳርጎታል፡፡ በመሆኑም በኤርትራ ተራሮችና የምስራቅ ኢትዮጵያ ጠረፎች የወደቀው አማራ፤ ልጆችን ያላሳዳጊና ያለመካሪ፤ አባቶችን ያለጧሪ፤ አስቀርቷል (Chege ፣ 1979፣374፤ Young ፣ 1996፣ 106)፡፡ በአጠቃላይ እኤአ የ1974ቱ የኢትዮጵያ አብዮት፤ የቀይ ሺብር ዘመቻ፤ የሶማሌ ወረራ፤ የራዛ ዘመቻ፤ የቀይ ኮከብ ዘመቻና በመሳሰሉት ታሪካዊ ክስተቶች ምክንያት በኢትዮጵያ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ለውጥ ማምጣት የሚችለው የአማራ ትውልድ ጠፍቷል፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ታሪካዊ ጥፋቶች የተረፈው የአማራ ወጣት ደግሞ ፖለቲካና ኤሌክትሪክን በሩቅ ብሎ ከኢትዮጵያ የፖለቲካ ስልጣንና የአመራር ቦታ ራሱን አግልሏል፡፡ እነዚህ ታሪካዊ ሁነቶች በአማራ ልሂቅ ላይ ከፍተኛ የትውልድ ክፍተት አስከትለዋል፡፡

ከሰብአዊ ጉዳቱ ባሻገር አማራ፤ ለንጉሱ ውድቀት ምክንያት የሆነው የወሎ ረሃብ ያደረሰበት ጉዳት እንዳለ ሆኖ፤ በድህረ አብዮት ኢትዮጵያ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ድቀት ደርሶበታል፡፡ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ አማራን በኢኮኖሚ ማድቀቅ የተጀመረው ገና የወታደራዊው መንግስት ወደ ስልጣን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ ደርግ ስልጣን በያዘ ማግስት ከመለሳቸው ጥያቄዎች አንዱ መሬት ላራሹ ነው፡፡ የዚህ ጥያቄ መመለስ ወቅታዊና ተገቢ ቢሆንም የአፈፃፀም ችግሮች ታታሪ ገበሬዎችንና ሃብት ፈጣሪዎችን እንደጎዳ እሙን ነው፡፡እንደሚታወቀው በድህረ ጣሊያን የንጉሱ ዘመን ከተመዘገቡ ለውጦች አንዱ መሬትን የግል ሃብት ማድረግ ሲሆን ይህም በመጨረሻዎቹ የንጉሱ 15 ዓመታት የአገዛዝ ዘመን ከፍተኛ የመሬት ሽያጭ እንዲከናወን አድርጓል (Bahru፣ 2002፣192)፡፡ በመሆኑም ግለሰቦች ሃብታቸውን መሬት ላይ አውለዋል፡፡ ግብርና በተለይ የእርሻ ግብርና ዋና

መተዳደሪያው የሆነው የአማራ ህዝብ ሃብትን መሬት ላይ የማስቀመጥ ባህሉ ከፍተኛ ነው። በወቅቱ መሬት የሃብት መገለጫ ስለነበር ባላቸው የትምህርት ደረጃ (የሃይማኖትም ይሁን ዘመናዊ) በመንግስት መስሪያ ቤቶችና በቤተ-ክህነት ተቀጥረው የሚያገለግሉ ግለሰቦች ከሚያገኙት የአግልግሎት ክፍያ (ደመወዝ) ወደ መሬት ቀይረው ማካበታቸው እሙን ነው። እንደሚታወቀው አርበኞችና የአርበኛ ቤተሰቦች ለአገር ነፃነት ለከፈሉት መስዋዕትነት ይከፈላቸው የነበረው የደም ዋጋ መሬት ነበር (Bahru፣ 2002፣192)። ስለሆነም ባግባቡና ያላግባብ የመጣ የመሬት ሃብትን የማጣራት ስራ ሳይሰራ ሁሉም መውረሱ የአማራን ህዝብ በምጣኔ ሃብት እንዳደቀቀው ጥርጥር የለውም። በተለይ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶች፤ ታላላቅ ኢንዱስትሪ፤ ፋይናንስና የንግድ ተቋሞች መወረስ (Clapham ፣ 1987 ፣ 152-153) የዘመናዊነትን መስፋፋት ተከትሎ ወደ ከተማ የተመመውን የአማራ ህዝብ በአንድ ሌሊት ወደ ድህነት ቀይሮታል። አስናቀ እንግዳ እንደፃፈው "ደርግ ጨቋኝና በዝባዢ እያለ ያለ ልዩነት የድሆችን ቤት ጭምር መውረሱን ኢህአፓ በልሳኑ ተቃውሞታል (አስናቀ፣መጋቢት 1994 ዓ.ም፣ 206)። ከሰብአዊና ኢኮኖሚያዊ ድቀት በተጨማሪ አማራ እንዲዳከም ያደረገው የባህል ስብራት ነው። ዶናልድ ሌቨን እንደፃፈው አማራ በመሬቱ (በርስቱ)፤ በዘመዱ፤ በሚስቱ፣ በእምነቱ ወዘተ. ለሚመጣበት ጠላት ተመጣጣኝና ከዚያ በላይ የሆነ የአፀፋ ምላሺ መስጠት ተገቢ መሆኑን ለታዳጊ ልጆቹ እየነገረ ያሳድጋል። ወጣቶች በልጅነት ዕድሜያቸው በዱላና በድንጋይ የመከላከልና የማጥቃት ስልት ይለማመዳሉ። ወኔ ቀስቃሺ ቀራርቶ/ሺለላ እና ፍከራ እንዲያዜሙ፤ ጀግኖችን የሚያወድሱ ግጥሞችን እንዲሸመድዱ ይበረታታሉ (Levine ፣ 2005-2006 ፣ 166)። የክፉ ቀን ጎበዝ በአለቃው ይሸለማል፤ በአዝማሪዎችና በአጠቃላይ በህዝቡ ይሞገሳል (Levine ፣ 2005-2006 ፣ 169)። ይህ ራስን ከአደጋ ለመጠበቅ የሚያዘጋጅ ጠንካራ ባህላዊ እሴት ደርግ ወደ ስልጣን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ እየተሸረሸረ መጥቷል። በመጀመሪያ በደርግ የሶሻሊስት ፖሊሲ መሬት የመንግስት ሆነ፤ የግል ሃብት ማካበትም በገደብ ተወሰነ። ስለሆነም ልጆች በጥንካሬና በጀግንነት እንዲጠብቁት የሚነገራቸው የግል ርስት/ሃብት የለም። ኃይማኖትም ቢሆን የኋላቀርነት ምልክት ተደርጎ እንዲዳከም ተሰብኳል። ደርግ ሃብታሞችንና ጠንካሮችን ሃብታቸውን ወርሶ፤ ትጥቃቸውን አስፈትቶ ሁሉንም እኩል ድሃና እኩል ደካማ ስላደረጋቸው ውድድርም የለም፤ የዚያኑ

ያክል የማጥቃት ሙከራም፤ የመጠቃት ስጋትም አልነበረም፡፡ ይህ ሥርዓት የአማራ ታዳጊዎች አባቶቻቸው መሳሪያ ሲወለውሉ፤ ኢላማ ሲሞክሩ፤ ጀግኖችን ሲያወድሱ እያዩና እየሰሙ የሚያድጉበትን ነባራዊ ሁኔታ አጥፍቶታል፡፡ ይህ የባህል ክፍተት ታዳጊ ልጆች ለርስት፤ ለሃብት፤ ለክብርና ነፃነት የመሞትን ዋጋ በአግባቡ ሳይረዱ፤ የህዝብን ክብርና ነፃነት ለማስጠበቅ የሚያስፈልጋቸውን የአቅም ብቃት፤ ወኔና ፍላጎት ሳያዳብሩ እንዲያድጉ አድርጓቸዋል፡፡ በደርግ ዘመን የአማራ ሰብዓዊ፤ ቁሳዊና ባህላዊ ውድመት ያለ ምንም ማቋረጥ ቀጥሏል፡፡ ከመጀመሪያዎቹ የደርግ ዓመታት በኋላ የአማራ ችግሮች የሚመነጩት ከደርግ የሶሻሊስት ፖሊሲዎች በተጨማሪ ከብሄርተኛ ግንባሮች የነፃነት ትግል ነው፡፡እንደሚታወቀው ከቀይ ሽብርና ከአሲምባው ጭፍጨፋ በኋላ የኢህአፓ ሰራዊት ይንቀሳቀስ የነበረው በሰሜንና ምዕራብ ጎንደር አካባቢ ነበር፡፡ የኢህአፓን መሰንጠቅ ያበሰረው የዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ህቡዕ ማእከል በለሳ በመሸገው የሰራዊቱ አባላት ነበር የተመሰረተው (ፅናት፣ 1993 ዓ.ም፣ 68, 71,151-152)፡፡ እኤአ ጁን 1980 ሳህላ ከሚባለው ስፍራ ላይ በተደረገው የሰራዊቱ ስብሰባ የዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ህቡዕ ማእከሉ ከኢህአፖ የተገነጠለ መሆኑን ይፋ አደረገ፡፡ ቀደም ሲል በተደረገ ውይይት ወደ አርማጭሆ ማፈግፈግ እንደ አማራጭ የቀረበ ቢሆንም ሰራዊቱ ማፈግፈግ ያለበት ወደ ትግራይ መሆኑን ገልፆ በዚህ የማይስማማ ትጥቁን አስረክቦ ወደ ደርግ ወይም ወደ ኢህአፓ መቀላቀል እንደሚችል አማራጭ ሰጠ (ከላይ የተገለፀው፣79፣ 82-83)፡፡ወደ ትግራይ የገባው የኢህአፓ ተገንጣይ ቡድን በማፈግፈግ ላይ እንዳለ ከህውሃት ጋር የሚወያይ ተወካይ እንደላከና ከዚያ በፊት ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደሌለው ቢገልፅም (ከላይ የተገለፀው፣80) ቀደም ያለ ሚሥጥራዊ ምክክርና ስምምነት እንደነበር ጠቋሚዎች አሉ፡፡ ለዚህ አስረጂ ይሆን ዘንድ ፅናት፡ የብሄረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ የተጋድሎ ታሪክ ከሚለው መፅሀፍ ላይ የተወሰደውን አንቀፅ እንይ፡፡

በ1972 ዓ.ም ወደ ሪጂን 1 ተጠርተው ሄደው የነበሩ 2 የበለሳ ሃይሎች ወልቃይት ላይ በተደረገው የኢህአፓና የህውሃት ጦርነት ላይ እንዲሳተፉ ትዕዛዝ ተሰጥቷቸው አንዷ ሃይል አሻፈረኝ ብላ ወደ ኋላ ስትመለስ ሌላዋ ሃይል በጉዳዩ ላይ ባደረገቺው ውይይት በመሃሏ ልዩነት ስለተነሳ ከሁለት ተከፍላ ከነበራት 55 አባላት 22ቱ ከሃይሏ ተገንጥለው ወደ በለሳ ተመልሰዋል፡፡ ይህቺ ጋንታ በበለሳ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ታሪክ ውስጥ ጋንታ 22 ተብላ ትጠራለች(ከላይ የተገለፀው፣85)፡፡

ይህ አንቀፅ የሚያስረዳን በኢህአፓ ውስጥ ተፀንሶ የነበረው ተገንጣይ ቡድን ገና በለሳን ከመልቀቁ በፊት ጀምሮ ህውሃትን እንዲያጠቃ የሚሰጠውን ትዕዛዝ ለመፈፀም ፈቃደኛ አለመሆኑን ነው፡፡ ቀደም ሲል ከአሲምባ ወግቶ ያባረረው ኃይል አሁንም ወልቃይትን ሊነጥቀው ሲመጣ ተገንጣዩ ቡድን አንዋጋም የሚል አቋም እንዴት ሊይዝ ቻለ? በተጨማሪም ከጎረቤት ሱዳን የሚዋሰነውን የአርማጭሆና የወልቃይትን ወታደራዊ ጠቀሜታ ትቶ ወደ ትግራይ መሄድን መምረጡስ ለምን ይሆን? እዚህ ላይ አስገራሚው ጉዳይ ህውሃት ወደ ጎረቤት አገር መውጫ ይሆነው ዘንድ ወልቃይትን ለመያዝ ሲሯሯጥ ተገንጣዩ ቡድን የመመለስ ፍላጎቱን ሳይገልፅ ጥሎለት ወደ ትግራይ መግባቱ ህቡዕ ማእከሉ ከህውሃት ጋር የቀደመ ስምምነት ሳይኖረው እንደማይቀር ያስጠረጥራል፡፡ በመጨረሻም ኢህዴንን መስርቶ ወታደራዊ ትግል ሲጀምር እንኳ ወደ ወልቃይትና አርማጭሆ አላማተረም፡፡ ይልቁንስ ከትግራይ በስተቀር ወደ ሌላ መፈናፈኛ የሌለውን የዋግ አውራጃን ነው ነፃ መሬቱ አድርጎ ትግል የጀመረው (Vaughan፣2003፣ 241)፡፡ ይህም የህውሃት ጥገኛ ሆኖ እንዲኖር ሳያደርገው አልቀረም፡፡

ሌላው አጠራጣሪ ጉዳይ ደግሞ ተገንጣዩ ቡድን የርዕዮት ልዩነቱን “ያስታረቀበት” መንገድ ነው፡፡ ኢህአፓ የብሄር ብሄረሰቦችን የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል እንደ መርህ የሚቀበለው ቢሆንም፤ የኢትዮጵያ ችግር የሚመነጨው ከመደብ ጭቆና ነው ብሎ ያምን ነበር (Tesfaye፣2005-2006፣ 57-58)፡፡ በአንፃሩ የኢትዮጵያ ተቃርኖ የሚመነጨው በጭቁን ብሄር ብሄረሰቦች ላይ ከተጫነው “የአማራ መንግስታዊ የበላይነት” ነው ብሎ በማመን ፤ህውሃት ከደርግ ጋር መፋጠጥ ያለባቸው ብሄር ተኮር ንቅናቄዎች ብቻ ናቸው የሚል አቋም ነበረው (Young፣1996፣ 114)፡፡ ኢህአፓንም አሲምባ ላይ የወጋው በዚሁ እሳቤ ነበር፡፡ አሁን ኅብረ-ብሄራዊው ኢህዴን በምን አግባብ ብሄርተኛው ህውሃት እንዲያደራጀው ጠየቀው? ህውሃትም ቢሆን ኅብረ-ብሄራዊው ኢህዴንን በነፃ መሬቱ እንዲመሰረት የፈቀደው ምን ቢያገኝ ነው? ብለን ስንጠይቅ መረጃዎች የሚያሳዩት ህውሃት አቋሙን ለውጦ ሳይሆን የኢህአፖ ተገንጣይ ከስም በስተቀር የብሄርተኛውን መስመር ለመከተል መስማማቱን ነው፡፡ የምርምር ስራዎች እንደሚያሳዩት በህውሃትና ኢህዴን መካከል የርዕዮትና የፖሊሲ ልዩነት የለም (Paulos ፣2003፣14)፡፡ በመሆኑም ከዚህ ትብብር ህውሃት አትራፊ ነበር፡፡ የተወሰኑትን

ለመጥቀስ ያክል ህውሃት በኢህዴን መመስረት የኢህአፓን መፈረካከስ እውን አድርጓል፡፡ በዚህም አንድ ጠንካራ ተቀናቃኙ የሆነ ህብረ-ብሄራዊ ፓርቲ (ኢህአፓን)፤ የፖሊሲው አስፈፃሚ በሆነ ህብረ-ብሄራዊው ኢህዴን ለመቀየር ችሏል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ መገንጠሉን ተከትሎ በመጣው የኢህአፓ መዳከም ህውሃት በወልቃይት በኩል በቀላሉ የውጭ በርና ወታደራዊ ጠቀሜታ ያለው መሬት ለማግኘት ችሏል፡፡ ሶስተኛ ህውሃት በጣም በሚያስፈልገው በወልቃይት በኩል ትኩረት ሲያደርግ በደቡብ ትግራይ (በተምቤንና ማይጨው) በኩል ለሚነሳበት የደርግ ጥቃት ኢህዴንን ጠባቂ ዘብ አግኝቷል፡፡

የኢህዴን መመስረት ለአማራ ህዝብ ምን ይዞለት ወይም ምን ይዞበት መጣ የሚለውን መዳሰስ አስፈላጊ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ኢህዴን የአማራ ፓርቲ አይደለም፡፡ ከላይ ከላይ ሲታይ የኢትዮጵያ ህዝቦች ፓርቲ፤ ጠለቅ ብልን ስንመረምር ደግሞ ብሄርተኞች የመሸጉበት ፓርቲ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በመሆኑም ለአማራ ከትግሬው፤ ከኦሮሞው ወዘተ. የተለየ ተቆርቋሪ አይደለም፡፡ ስለሆነም ጠቃሚ ነገር ቢኖረው እንኳ ኢህዴን ለአማራ ህዝብ ከማንኛውም የኢትዮጵያ ብሄር፤ ብሄረሰብና ህዝቦች (የራሳቸው ነፃ አውጪ ግንባር ካላቸው ጭምር) በተለየ መልኩ በተቆርቋሪነት ለማገልገል ተፈጥሯዊ ስሪቱ አይፈቅድለትም፡፡ ከዚህ በተፃራሪ ግን አማራ ጠላቴ ነው ብሎ በማንፌስቶው ካፀደቀው ህውሃት ጋር አጋርነት ሲፈጥርና ህውሃትን ሲያግዘው፤ ሲያጎለምሰው የአማራ ችግርና መከራ እየሰፋ ነው የመጣው፡፡ በመጀመሪያ ኢህዴን ዋግ አውራጃን ነፃ መሬቱ አድርጎ ወደ መሃል ወሎና ጎንደር ሲስፋፋ አካባቢው ወደ ጦርነት ቀጣና ተቀይሯል፡፡ በዚህም ምክንያት ነዋሪዎች ተሰደዋል፤ ንብረታቸው ወድሟል፤ ተዘርፏል፡፡ የመሰረተ-ልማት አውታሮች በጦርነት ወድመዋል ወይም በህውሃት ተዘርፈዋል፡፡[4] ከምንም በላይ ኢህዴን የአማራ ክፍለ ሃገሮችን ነፃ መሬት አድርጎ መንቀሳቀሱ በብሄርተርተኞች ዘመን የአማራ ብሄርተኝነት እንዳይወለድ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የአማራ ህዝብ ለሁለት ተቃራኒ ኃይሎች፤ ለደርግና ለኢህዴን፤ ልጆቹን ለመገበር ተገድዷል፡፡ የኤርትራ ነፃ አውጪ ግንባርን፤ ህውሃትንና ኢህዴንን ሌሎችንም ቤሄርተኛ ግንባሮችን በገንጣይና አስገንጣይ የፈረጀው ደርግ ለመደበኛም ሆነ ለብሄራዊ ውትድርና የሰው ሃይል ምንጩ በዋናነት የኤርትራን መገንጠልም ሆነ የኢትዮጵያን መፈረካከስ የማይፈልገው

[4] የቃል መረጃ አቀባዮች፤ አቶ አዝመራው ነጋሺ፤ አቶ ወልዱ አባተ፤ኮሎኔል አባተ መኮንን

የአማራ ህዝብ ነው፡፡ በተመሳሳይ ነባር ታጋዮች እንደተናገሩት ኢህዴንን ከተቀላቀሉ አንዳንድ ፈቃደኛ የደርግ ምርኮኞች ውጭ ድርጅቱ ሰራዊት የሚመለመለው ከአማራው ማህበረሰብ በተለይም ከጎንደርና ሰሜን ወሎ ነበር፡፡ ኢህአዴግ ወደ መሃል አገር እየገሰገሰ ሲመጣ ደግሞ ከደቡብ ወሎና ከሰሜን ሸዋ መመልመል ችሏል፡፡[5]ከሰው ሃይል አቅርቦት በተጨማሪ ለአማፂያኑ ሰራዊቱ ስንቅ የሚያቀርበው፤ መንገድ የሚመራው፤ ጓዝ የሚሸከመው፤ በፍላጎትም ሆነ በግዳጅ፣ የአማራ ገበሬ ነበር፡፡ ምናልባትም አማራን በጠላትነት የፈረጀውና የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክን የመመስረት ዓላማ አንግቦ የተነሳው ህውሃት፤ ሌሎች ምክንያቶች እንዳሉ ሆኖ፤ ብሄርተኝነቱን በኢህዴን-ኢህአዴግ ኅብረ-ብሄራዊነት ካባ ደብቆ ባይመጣ ኖሮ የአማራን ህዝብ ድጋፍ ማግኘት አይችልም ነበር፡፡ ካለ አማራ ድጋፍ ደግሞ ደርግን ማሸነፍ አይችልም ነበር፡፡ በተጨማሪም ኢህዴንን ሳይዝ ወደ አማራ ክፍለ ሃገሮች ለመግባት ቢሞክር ኖሮ ጦርነቱ ያለ ምንም ጥርጥር የማንነት ቅርፅ ይይዝ ነበር፡፡ በዚህ ዓይነቱ ጦርነት ደግሞ ህውሃት ከአማራ መሬት መውሰዱ ይቅርና በትግራይ የሚኖረውም ህልም ዕውን የመሆኑ ጉዳይ አጠራጣሪ ነው፡፡ የወልቃይት፤ ጠገዴ፤ ጠለምትና ራያ፤ ፍላጎታቸውም መልስ የሚያገኘው በዚያኑ ወቅት በሚደረግ ትግል ውጤት ይሆን ነበር፡፡ እነዚህ ቦታዎች በህውሃት ይዞታ እንዲገቡ ህዝቡን ያዘናጋው የአማራ ፓርቲ ሳይሆን በአማራ መሬት ይንቀሳቀስ የነበረው ኢህዴን በመሃል በመሰንቀሩ ነው፡፡[6]

መረጃዎች እንደሚያሳዩት ህውሃት እኩልና ተገዳዳሪ ኅብረ-ብሄራዊም ሆነ ብሄርተኛ ፓርቲ እንዲወጣ አይፈልግም፡፡ ለዚህም ጥሩ ማሳያ ኢህዴንንና ኦነግን ያሳነሰበት የፖለቲካል ሴራ ነው፡፡ ቀደም ሲል ኢህዴን በህውሃት መስመር እንደገባና ጠንካራ የኅብረ-ብሄራዊ ፓርቲ አቋም እንደሌለው ተጠቅሷል፡፡ ያም ሆኖ ህውሃት ኢህዴንን ይበልጥ ለማሳነስ በቀጣይነት ይሰራ ነበር፡፡ እኤአ በ1990 የኦሮሞን ህዝብ እንዲያታግል በሚል ስም በኢህዴን ስር የነበሩ የኦሮሞ ታጋዮችን (ከኢህዴን ጋር ለመታገል ፈቃደኛ የነበሩ ምርኮኛ ወታደሮችን) ነጥሎ የኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦህዴድ) እንዲመሰረት አደረገ፡፡ኢህዴን የኦሮሞን ህዝብ ሳያሳትፍ ጠንካራ ህብረ-ብሄራዊ ፓርቲ ሊሆን አይችልም፡፡ የኦሮሞና ሌሎች ብሄር ታጋዮች ወደየማንነታቸው መቀላቀል፤ በአንድ በኩል

[5]የቃል መረጃ አቀባዮች፤ አቶ አዝመራው ነጋሺ፤ አቶ ወልዱ አባተ፤ኮሎኔል አባተ መኮንን፤ ኮሎኔል ባምላኩ አበበ፡፡

[6]የቃል አቀባዮች፤ አቶ የኔሰው ገረመው፤አቶ ታለ ምንተስኖት፤አቶ ጋሻው ተሰማ፡፡

ኢህዴን የአማራ ፓርቲ እንዲመስል አድርጎታል። ይሁን እንጂ ከኢህዴን ጋር መቆየት የሚፈልግ ማንኛውም ተጋይ ብሄሩ ከየትም ይሁን ከየት በሙሉ እንዲለቅ ስላልተገደደ፤ ትግሬን ጨምሮ ከየብሄሩ ተሳታፊ አባላትን እንዳቀፈ ስለነበር[7]የአማራ ፓርቲ መሆንም አልቻለም። በዚህም የተነሳ ኢህዴንን ከሁለት የወጣ ጎመን እንዲሉ ህብረ-ብሄራዊውም ሆነ ብሄርተኛ እንዳይሆን አደረገው።

ከላይ እንደተጠቀሰው የኦሮሞን ህዝብ የሚያታግሉ ሁለት ድርጅቶች ማለትም ኦህዴድና ኦነግ እንዲኖሩ በማድረግና አላስፈላጊ ፉክክር ውስጥ በማስገባት ህውሃት አትራፊ ሆኗል። የኦህዴድ መመስረት የኦነግን ሃይል አዳክሞለታል (Joireman ፣ 1997 ፣ 394 ፤ Vaughan ፣ 2003፣31)። በተጨማሪም የኦነግና ኦህዴድ የርስበርስ ሺኩቻ እንዳለ ሆኖ የኦሮሞ ኃይሎች ከኢህዴን መውጣትና ሁለተኛውን የኦሮሞ ብሄርተኛ ፓርቲ መመስረታቸው የኦሮሞ ህዝብ ከህብረ-ብሄራዊ አታጋይ ፓርቲ ውጭ እንዲሆንና በብሄር መንገድ እንዲጓዝ አድርጎታል። ህውሃት ከዚህ በኋላ በእሱ የበላይነት የሚመራውን የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ)ን እኤአ በ1989 ፈጠረ (Beken ፣ 2015 ፣ 152)። የግንባሩ አባላት ህውሃት፤ ኦህዴድ፤ ኢህዴንና የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መኮንኖች አብዮታዊ ንቅናቄ (ኢዴመአን) ነበሩ። የኢዴመአን መስራቾች በሻቢዕያ፤ ህውሃትና ኢህዴን የተማረኩ መኮንኖች በመሆናቸው ለህውሃት ከመታዘዝ ያለፈ ሚና አልነበራቸውም። ያም ሆኖ ኢዴመአን ብዙም ሳይጓዝ ከድል በኋላ ከስሟል (ባህሩ፣1983፣277)። በዚህ መልኩ ህውሃት በኢህአዴግ ውስጥም ሆነ ከኢህዴግ ውጭ ጠንካራና ወሳኝ ፓርቲ ለመሆን በቃ።

ለማጠቃለል ያክል በደርግ ዘመን የአማራ ህዝብ ከፍተኛ ሰብአዊ፤ ኢኮኖሚያዊ፤ ማህበራዊና ባህላዊ ድቀት ደርሶበታል። በመጀመሪያ አብዮቱ በፀረ-ፊውዳል ዘመቻው የአማራ መኳንንትና መሳፍንትን በልቷል። በሁለተኛ ደረጃ ከላይ እንደተገለፀው የኤርትራ፤ የትግራይ፤ የኦሮሞ ወዘተ. ወጣቶች በረሃ ወርደው እራሳቸውን እያደራጁ ባሉበት ወቅት ከደርግ ጋር የተፋጠጠው የአማራ ወጣት በቀይ ሺብር ጅምላ ጭፍጨፋ ጠፍቷል። ቀሪ የአማራ አባቶችና ልጆች ደግሞ ከሁለቱም ጎራዎች ማለትም በአንድ በኩል ከአስገንጣይ[8]

[7]የቃል መረጃ አቀባዮች፤ አቶ አዝመራው ነጋሺ፤ አቶ ወልዱ አባተ፤ኮሎኔል አባተ መኮንን፤ ኮሎኔል ባምላኩ አበበ።

[8]ደርግ ሻቢዕያን ገንጣይ፤ ህውሃት፤ ኢህዴንና የመሳሰሉትን ብሄርተኛ ፓርቲዎች ደግሞ አስገንጣይ ብሎ ይጠራቸው ነበር።

(ህውሃት፣ ኢህዴንና የመሳሰሉት) በሌላ በኩል ከደርግ ጋር በመሰለፍ ህይዎታቸውን አጥተዋል፣ አካላቸውን አጉድለዋል። አማራ በደርግ የሶሻሊስት ፖሊሲ የኢኮኖሚና የባህል ድቀት ደርሶበታል። በኢህዴን መሪነት ወደ መሃል አገር የገሰገሰው ህውሃት መራሹ የኢህአዴግ ሃይል የአማራ ክፍለ ሃገሮችን ማለትም ጎንደር፣ ወሎና ሸዋን የጦርነት አውድማ ስላደረጋቸው የኢኮኖሚና ማህበራዊ አውታሮች ወድመዋል፣ ተዘርፈዋል። ይህ የማያባራ ሰብአዊ ጭፍጨፋ፣ ኢኮኖሚያዊ ድቀትና ባህላዊ ስብራት እየደረሰበት፣ አማራ በዚህ ሰዓትም እንኳ ከችግር የሚያወጣውን መንገድ አልተለመም፣ ለመደራጀት አልሞከረም። ይልቁንም የንጉሱ ዘመን ወጣት አማራን በጨቋኝነት ከፈረጀው ብሄርተኛ ቡድን ወግኖ የወጣበትን ማህበረሰብና ራሱን በጨቋኝነት ይወነጅል እንደነበረው ሁሉ፣ የአሁኑ ትውልድም አማራ ጠላቴ ነው ብሎ በማንፌስቶው ካስቀመጠው ህውሃት ጋር ግንባር ከፈጠረው ኢህዴን ወይም አማራን በቀይ ሺብር ከጨፈጨፈውና በኢኮኖሚ ካደቀቀው ደርግ ጋር ነበር የተሰለፈው። ይህ ሃይል ለሁለቱ ተቃራኒ ሃይሎች አገልጋይ እንጂ ለአማራ ህዝብ ፋይዳ ያለው አላማና ግብ ያነገበ አልነበረም። ከድጡ ወደ ማጡ እንዲሉ ህውሃት ኢህዴንን ተጋብቶና የተገንጣይነት ባህሪውን በኢህአዴግ ደብቆ በመምጣቱ የደቀነለትን አደጋ ሳይረዳ የአማራው ኃይል ታላቅ ድጋፍ ቸሮታል። ይህም ለኢህአዴግ የመሃል አገር ጎዞውን አቅልሎለታል። ስለሆነም ትግራይን ነፃ ለማውጣት ከአስር ዓመት በላይ የፈጀበት ቡድን ትግሉን ሳብ አድርጎ ወደ አማራ ክፍለ ሃገሮች ባስገባ በሁለትና ሶስት ዓመታት ውስጥ ወደ ስልጣነ-መንበር ለመውጣት ችሏል። በዚህም ሂደት የአማራ ህዝብ ሳያቅድና በማንነቱ ሳይለይ ከጨፈጨፈው ደርግ፣ በጠላትነት በፈረጀውና በዕቅድ ሊያጠፋው ከተነሳው ህውሃትና ሌሎች መሰል ብሄርተኛ ቡድኖች አገዛዝ ስር ለመውደቅ በቅቷል። ለዚህ እንዲበቃም ያለ አላማና ግብ ትግል የወጡ የአማራ ወጣቶች ሚና ከፍተኛ ነበር።

**የብሄርተኞች አገዛዝ ዘመን**

የተማሪዎች ንቅናቄ የወለዳቸው የብሄር ግንባሮች አድገውና ጎልምሰው እኤአ በ1991 መንግስታዊ ስልጣን ላይ ተቆናጠጡ። ቀደም ሲል እንደተገለፀው የፖለቲካና ማህበራዊ ለውጥ ሊያመጣ የሚችለው የአማራ ልሂቅ በአብዮቱና በአብዮቱ ማግስት ስለተጨፈጨፈና ከጭፍጨፋው የተረፈው ደግሞ ፖለቲካና ኤሌክትሪክን በሩቅ ብሎ ራሱን ከፖለቲካው መድረክ ስላገለለ ብሄርተኛው ቡድን ያለ ጠንካራ ተቀናቃኝ ማዕከላዊ መንግስቱን

እንዲቆጣጠርና ያሻውን መንግስታዊ መዋቅር እንዲመሰርት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮለታል። ያም ሆኖ ግን ብሄርተኛው ቡድን የተጓዘበት የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ትግል በጨቋኝ ተጨቋኝ ትርክት ላይ የተመሰረተ ስለነበር፤ የአዲሱ መንግስት ምስረታ የአማራን ህዝብ ያካተተ አልነበረም። ለምሳሌ ያክል እኤአ ጁን 1991 ሰማኒያ ሰባት መቀመጫ ያለው የሽግግር መንግስቱ ምክር ቤት ሲቋቋም ትልቅ ቁጥር ካለው የአማራ ህዝብ የተወከለና ወንበር የተጋራ የፖለቲካ ፓርቲ የለም (Keller ፣ 1995 ፣ 630)። ይህ ችግር የተፈጠረው አማራ ቀደም ብሎ በማንነት ባለመደራጀቱ ብቻ ሳይሆን ተደራጅቶ እንዲወከል ስላልተፈለገ ጭምር ነው። ምክንያቱም ብዙዎቹ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ፓርቲ እንዲመሰርቱና በምክር ቤቱ እንዲወከሉ የተደረገው በሽግግር መንግስቱ መመስረት ዋዜማ ነው። እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ብገርታ ለመፍጠር የተሞከረው ደግሞ አማራ በኢህዴን ተወክሏል በሚል ነው። እርግጥ ነው ከ90 ፐርሰንት በላይ የኢህዴን ሰራዊት አማራ ነው (Paulos ፣ 2003 ፣ 14)። ይሁን እንጂ የፖለቲካ ክንፉ ኅብረ-ብሄራዊ መሰል እንጂ አማራን የሚወክል ብሄርተኛ አልነበረም። የፓርቲው ስያሜም ወደ ብአዴን አስከተቀየረበት እኤአ እስከ 1992 ድረስ ኅብረ-ብሄራዊ ነበር። አባልነትም ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ ክፍት ነበር።[9] ከስያሜም ለውጥ በኃላም ቢሆን የብሄር ድርጅት ነበረ ለማለት ያስቸግራል። በዚህም ሊሆን ይችላል ኢህዴን-ብአዴን-አዴፓ ቆሜለታለሁ ለሚለው የአማራ ህዝብ ጥቅምና መብት ሲታገልና ህዝቡን ሲያታግለው አይታይም። ድርጂቱ የአማራ ማህፀን አምጦ የወለደው ስላልሆነ ከአማራ ህዝብ ይልቅ ከሌሎች ብሄርተኛ ፓርቲዎች ጥብቅ ቁርኚት አለው።በመሆኑም ስብስቡ አትኩሮ የሚሰራው ስልጣንን ከቤተሰብና ዘመድ ላልሰፋ የማህበረሰብ ክፍል ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ደህንነት ማስጠበቂያ ይመስላል።

በሽግግር መንግስቱ የአማራን ዕጣ ፈንታ የሚወስኑ፤ ከብዙ በጥቂቱ፤ ሁለት ቁልፍ ጉዳዮች ተከናውነዋል። የመጀመሪያው የክልሎች ምስረታ ነው። በሽግግር መንግስቱ የተቋቋመው የድንበር አካላይ ኮሚሽን የተመሰረተው እኤአ ኦገስት 1991 ነው። ኢህአዴግን ጨምሮ 7 የፖለቲካ ፓርቲዎችን ያቀፈው ኮሚሽን አስር አባላቶች ነበሩት። እነዚህም 3 ከኢህአዴግ፤ 2 ከኦነግ፣ 1 ከጉራጌ፣ 1 ከሃድያ፤ 1 ከሃራሪ፤1 ከአፋርና 1 ከሶማሌ ናቸው

---

[9]የቃል መረጃ ሰጭዎች፤ አቶ አዝመራው ነጋሺ፤ አቶ ወልዱ አባተ፤ኮሎኔል አባተ መኮንን፤ ኮሎኔል ባምላኩ አበበ።

(Vaughan፣2003፣ 33)። በዚህ ውክልና የተፈፀመው የክልል ክፍፍል ፍትህ የጎደለው ነበር። የኢፍትሃዊነት ጥግ ማሳያው ደግሞ ኦነግ ያቀረበው የይገባኛል ጥያቄ ነው። ኦነግ ሸዋን ከሚገባው በላይ መሰልቀጡ ሳያንሰው "የታሪካዊ ባለቤትነት"ን አጣቅሶ ወሎ ይገባኛል የሚል ጥያቄ አንስቶ ነበር። አስገራሚው ነገር ደግሞ ለዚህ ጥያቄ ውደቅ መሆን ዋናው ምክንያት መሬት ላይ ያለው ነባራዊ እውነታ ሳይሆን ከሃድያ ተወካይ የተነሳው ተመሳሳይ ጥያቄ ነው። የሃድያ ተወካይ "የታሪካዊ ባለቤትነት"ን አጣቅሶ ባሌና አርሲ የሃድያና ሲዳማ መሆን ይገባቸዋል የሚል ተገዳዳሪ ጥያቄ ሲያነሳ እንደመፍትሄ የተወሰደው ሁለቱንም ጥያቄዎች ውድቅ እንዲሆኑ ማድረግ ነበር። የወሎ አማራ በእውነተኛ ማንነቱ የተካለለበት አጋጣሚም ይህ ነው። ለዚህ ጥያቄ መነሳት፣ የአሁኑ ወሎ በታሪክ ባለቤትነትም ቢሆን ቀደምት የአማራ መገኛ /ቤተ-አምሃራ/ መሆኑ ለኦነግ ተወካዮች ጠፍቷቸው ሳይሆን፣ ሁለት ምክንያቶች ገፊ እንደሆኑ እንረዳለን። አንደኛ የአማራን አለመወከል እንደ መልካም አጋጣሚ የመጠቀም ፍላጎት ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ አይሆንም እንጂ ቢሆንላቸው ወሎ የኛ ነው፣ አዲስ አበባ የኛ ነው፣ የሚሉት የኦሮሞ ፖለቲከኞች ሁል ጊዜ የታሪክ መነሻ ከነሱ መገኛ እንዲሆን የሚሹ በመሆኑ ነው። ያም ሆነ ይህ አማራ ባለመወከሉ ታሪካዊ ባለቤትነት የሚጠይቅባቸውን ይቅርና በወቅቱ የአማራ የሆኑ ሰፋፊ ግዛቶቹን አጥቷል።[10] በመሆኑም በሺግግር መንግስቱ ከፍተኛ ስልጣን የያዙት ህውሃትና ኦነግ በክልል አመሰራረቱ ልዩ ተጠቃሚ ሲሆኑ ውክልና የሌለው አማራ ደግሞ ከፍተኛ ተጎጂ ሆኗል።

የድንበር አካላይ ኮሚሺኑ ተግባር የክልሎችን ንድፍ ካርታ ማመላከት ሲሆን ፤ የክልሎችን የውስጥ ድንበር የማካለል ሥራ ለተደናባሪ የክልል መንግስታት የተተወ ነበር (Vaughan፣2003፣ 34)። ይህ ማለት የአማራን ድንበር የማካለል ኃላፊነት የወደቀው አማራን በማይወክለው ኢህዴንና በአጎራባች ብሄርተኞች ለምሳሌ ህውሃት፤ ኦነግ/ኦህዴድና በመሳሰሉት መካከል ነው። ከላይ እንደተገለፀው ኢህዴን ከህብረ-ብሄራዊ አፈጣጠሩ የተነሳ ለአማራ ከኦሮሞው፣ ከትግሬው፣ ከጉራጌው የተለየ ተቆርቋሪ አይደለም። ስለሆነም በድንበር ማካለሉ ላይ የአማራን ፍላጎት የሚያስጠብቅ አልነበረም። በመሰረቱ በአንድ በኩል ብሄርተኛ ቡድን ብሄሩን ወክሎ፣

[10]የቃል መረጃ አቀባዮች፤ አቶ አዝመራው ነጋሺ፤ አቶ ወልዱ አባተ፤ኮሎኔል አባተ መኮንን፤ ኮሎኔል ባምላኩ አበበ፤ አቶ የኔሰው ገረመው፤አቶ ታስ ምንተስኖት፤አቶ ጋሻው ተሰማ።

በሌላ በኩል ኅብረ-ብሄራዊ ፓርቲ ከሚታገልላቸው ብሄሮች መካከል አንዱን ወክሎ ፤ የሚያካሂዱት የድንበር ማካለል ስራ በመርህ ተቀባይነት የለውም፤ በተግባርም ፍትሃዊ አይሆንም። ከዚህ የባሰው ግን ከላይ የተጠቀሰው ሽውራራ ህግ እንኳ ተግባራዊ ሳይሆን ሁሉም ነገር በአንድ ቡድን የበላይነት መከወኑ ነው። መረጃዎች እንደሚያሣዩት የአማራና የትግራይ ክልሎች ድንበር የተወሰነው አማራን የወከለው መንግስት ተሳትፎ ሳይኖር ወይም የህዝብ ፈቃደኝነት ሳይጠየቅ ህውሃት በበየነው መሰረት ብቻ ነበር (አለሙ ካሳና ሲሳይ መንግስቴ፤2005፣7)። ከሌሎች ጎረቤት ክልሎች ጋር ለነበረው የድንበር ማካለል የህውሃት ተፅዕኖ ከፍተኛ እንደነበር እሙን ነው። በጥቅሉ የአማራ ማንነታቸው ጥያቄ ውስጥ የማይገባው የወልቃይት፤ ጠገዴ፤ ጠለምት፤ ራያ፤ መተከል፤ ደራና የሌሎችም አማራዎች አላግባብ በሌላ ክልል እንዲተዳደሩና ማንነታቸውን እንዲገፈፉ የተደረጉበት ምክንያት ከኢህዴን ፖለቲካዊ አፈጣጠር፤ ከህውሃት ፍፁም የበላይነትና ከአማራ አለመወከል ይመዘዛል። ሌላው አስገራሚው ነገር ከላይ የተገለፁት አብዛኞቹ የድንበር ማካለል ውሳኔዎች የተላለፉት ህገ-መንግስቱ ከመፅደቁ በፊትና ለማስመሰያ ያክል የሚያገለግል እንኳ ህጋዊ ማዕቀፍ በሌለበት ነው።

ሁለተኛው ቁልፍ ጉዳይ የህገ-መንግስት ቀረፃ ነው። የኢህአዴግ ህገ-መንግስት የማርቀቅ ስራ የተራዘመ ጊዜ ወስዷል (Tesfaye፣ 2005-2006፣ 62)። በመጨረሻም ልክ እንደ ሺግግር መንግስቱ ቻርተር ህገ-መንግስቱም የአማራ ህዝብ ባልተወከለበት እኤአ በዲሴምበር 1994 ፀድቆ ከኦገስት 21፣ 1995 ጀምሮ ስራ ላይ ውሏል (Abbink፣2011፣597)። የኢህአዴግ መንግስት መገለጫ የሆነው የብሄር ፌደራሊዝም ፅንሰ-ሃሳብ እኤአ ከጁን 1991 ጉባኤ በኋላ በታወጀው የሺግግር መንግስቱ ቻርተርም ሆነ እኤአ በዴሴምበር 1994 ፀድቆ ከኦገስት 1995 ጀምሮ ስራ ላይ በዋለው የፌደራል ህገ-መንግስቱ ሰፋ ባለ መልኩ በዝርዝር ቀርቧል (Abbink ፣ 2011 ፣ 597)። የብሄር ፌደራሊዝሙን ከሚቃወሙት ግንባር ቀደሙ አማራ ነው። የመላው አማራ ህዝብ ድርጅት ፌደራሊዝምን ሙሉ በሙሉ ተቃውሞ አሃዳዊ አስተዳደርን የመረጠ ቢሆንም፤ ፌደራሊዝምን የሚደግፉ የተለያዩ ብሄር ድርጅቶች ጭምር የፌደራል አወቃቀሩ በማንነት ላይ መሆኑንና በህገ መንግስቱ ዕውቅና የተሰጠውን የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብት እስከ መገንጠል ፅንሰ-ሃሳቦች ይቃወሙ ነበር። በዚህ ረገድ የአፋር

አብዮታዊ ዴሞክራቲክ አንድነት ግንባርና የጋምቤላ ብሄራዊ ዴሞክራቲክ ትብብር ተጠቃሽ ናቸው (Kidane፣2001፣ 22)። በእርግጥ የኢትዮጵያ ፌደራሊዝም በዓለም ህዝብ ዘንድ አግራሞትን የፈጠረ ነበር። ለምሳሌ ያክል አፍሪካዊያን ፖለቲከኞች፤ ምሁራንና ተማሪዎች ትዝብታቸውን የገለፁት እንዲህ ሲሉ ነበር።

We do not understand Ethiopian politics. How can they go and institutionalize tribalism. This was the one country in Africa with a non-colonial history, an indigenous state that had some unity and a centralist tradition, and now they follow us and go back to fragmentation (Abbink፣2011፣599).

የብሄረሰቦችን እኩልነት በማቀንቀንም ይሁን የንጉሱንም ሆነ የደርግን ስርዓቶች በመዋጋትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሰፍን በመሻት ረገድ የአማራ ህዝብ ቢበልጥ እንጂ ከብሄርተኞቹ ያላነሰ ድርሻ ነበረው። ጭቆናን በመታገል ረገድ በብሄርተኞቹና በአማራ ህዝብ መካከል የነበረው መጠነኛ ልዩነት አደረጃጀት እና ርዕዮት ላይ ነው። ብሄርተኛው ቡድን በማንነት ተደራጅቶ የ"ብሄር ጭቆና"ን ሲታገል፤ አማራ ደግሞ በኅብረ-ብሄራዊ አደረጃጀት የመደብም ሆነ የብሄር ጭቆናን ታግሏል። የ"ብሄር ጭቆና"ን ያቀነቀነና ወገኑን የወነጀለ አማራም ነበረ። ከከሸፈው መፈንቅለ መንግስት ሙከራ ጀምሮ በተማሪዎች ንቅናቄና ሌሎች አደረጃጀቶች ውስጥ አማራ ያከናዎናቸውን ፀረ-ፊውዳል፤ ፀረ-ካፒታልስትና የብሄር እኩልነትን ተጋድሎ ስናይ፤ ኢትዮጵያዊያን እኩል የሚኖሩባት አገር የመፍጠር ራዕይ እንደነበረው እንረዳለን። ነገር ግን የብሄርተኛው ቡድን የተከተለው የትግል ስልት አማራን በሃሰት ትርክት መወንጀል ነው። ለምሳሌ ያክል የአማራን ትግል በማሳነስ ድልን ጠቅልሎ ለመውሰድ ከነበራቸው ፍላጎት አማራን በጠቅላይነትና ግላዊነት ይወነጅሉት ነበር። በመሆኑም ብሄርተኛው መንግስት የነበሩ ችግሮችን ከማስተካከል ይልቅ አማራን የማያካትት እና ኢፍትሃዊ የሰፈነበት ሥርዓት ግንባታ ላይ ተጠመደ። አማራን ከቅጥር፤ ከምርጫ፤ ከዳኝነትና ከፖለቲካ ስልጣን ማግለልን ሥራየ ብሎ ተያያዘው። ከዚያም ጨቋኝ፤ ነፍጠኛ፤ መጤ፤ ሰፋሪ የሚል ስያሜዎች በመስጠት ከቃላትና አካላዊ ጉዳት ያለፈ ሁከት በመፍጠር ከክልሉ ውጭ ያሉ አማራዎችን ማፈናቀል የአደባባይ ተግባሩ ሆነ (Abadir፣ 2018፣20)። በጥቅሉ ብሄርተኞቹ በተለይ ህውሃትና ኦነግ ሁሉም ኢትዮጵያን እኩል የሚሳተፉባትን ሳይሆን ከቻሉ በነሱ የበላይነት የምትዘወር ኢትዮጵያን ካልሆነ ደግሞ የራሳቸውን አገር መፍጠርን ግብ አድርገው ተጓዙ።

በመጨረሻም ህውሃት ኦነግን ከመንግስታዊ ሥልጣን በመግፋት የበላይነት ፍላጎቱ ለማሳካት ቻለ፡፡

ህውሃት የበላይነቱን ለማስቀጠል ያሰጋኛል ብሎ የሚያስበው ከማንም በላይ የአማራን ህዝብ ነው፡፡ ለዚህም ይመስላል አማራ በሌሎች ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እንዲጠላና የሥርዓታዊና መዋቅራዊ ጥቃት ሰለባ እንዲሆን አበክሮ ሰርቷል፡፡ ይህ ነባራዊ ሁኔታ የአማራን መገለል፣ መሳደድና ወከባ ከጊዜ ጊዜ እንዲጨምር አድርጎታል (ከላይ የተጠቀሰው)፡፡ የጥቃቱ ስፋትና ግዝፈት ለዘመናት በህብረ-ብሄራዊ ትግል ይታወቅ የነበረው አማራ ዘግይቶም ቢሆን መስመሩን እንዲፈትሽ አስገድዶታል፡፡ በዚህም የብሄርተኛውን ጥቃት፣ እሾክን በሾክ እንዲሉ፣ በተመሳሳይ አደረጃጀት ካልሆነ በስተቀር በህብረ-ብሄራዊ አደረጃጀት መቀልበስ እንደማይቻል በመገንዘብ የመጀመሪያውን አማራዊ ፓርቲ የመላው አማራ ህዝብ ድርጂት (መአህድ)ን እኤአ በጃንዋሪ 1992 መሰረተ (Joireman፣1997፣ 395)፡፡ መአህድ አፈጣጠሩ ብሄርተኛ ይሁን እንጂ ዋነኛ የፖለቲካ ግቡ የኢትዮጵያን አንድነት ኤርትሪያን ጨምር ማስጠበቅ ነበር፡፡ በመሆኑም የብሄር ብሄረሰቦችን ራስን ዕድል በራስ መወሰን መብት እስከመገንጠል የሚለውን ሃሳብ ይቃወማል፡፡ የኢህአዴግ ፖሊሲ የኢትዮጵያን አንድነት የሚያፈራርስ እንደሆነ ያምን ነበር፡፡ መአህድ የሺግግር መንግስቱ በአንድ ፓርቲ የበላይነት ተፅዕኖ ሥር ወድቋል በሚል እምነት በአዲሱ ህገ-መንግስት የማርቀቅ ስራም ሆነ ህገ-መንግስታዊ ጉባኤ ምርጫ ላይ አልተሳተፈም፡፡ ያም ሆኖ ግን ጠንካራ የመንግስት ተቃዋሚ ነበር(ከላይ የተጠቀሰው)፡፡

የብሄርተኛው መንግስት የአማራን መደራጀት እንደ ታላቅ ስጋት ስለሚያየው፣ የመአህድን እንቅስቃሴ ለማኮላሸት ወይም ለማቀጨጭ የተለያዩ እንቅፋቶችን መፍጠሩን የተያያዘው ገና ከጥዋቱ ነበር፡፡ በመጀመሪያ ህውሃት ቀደም ሲል የብሄርም ሆነ ህብረ-ብሄራዊ ፓርቲ ቁመና እንዳይኖረው አድርጎ ያስቀመጠውን ኢህዴንን፣ የአማራን መደራጀት ባየበት ወቅት ብሄረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ በሚል የስም ለውጥ ብቻ የመአህድ ተገዳዳሪ ኃይል እንዲሆን አድርጎ አስቀመጠው፡፡[11] ብአዴን ከስያሜ ለውጥ በስተቀር ተልዕኮና ራዕዩ ከኢህዴን-ኢህአዴግ የተቀዱ በመሆናቸው ለአማራ ህዝብ አዲስ ነገር የሚያመጣ አልነበረም፣ አላመጣምም፡፡ የድርጅቱ ስያሜ መቀየር ግን የአማራን

---

[11]የቃል መረጃ ሰቀባዮች፤ አቶ አዝመራው ነጋሺ፤ አቶ ወልዱ አባተ፤ኮሎኔል አባተ መኮንን፤ ኮሎኔል ባምላኩ አበበ፡፡

ህዝብ የመከፋፈልና የአማራውን ፓርቲ መአህድን የማዳከም ሚናው ቀላል አልነበረም፡፡ ብሄርተኛው ቡድን አማራን ለመከፋፈልና ለማዳከም የተጠቀመበት ሌላው ስልት በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ንዑስ ማንነት ያላቸውን ብሄረሰቦች የልዩ ዞን አስተዳደር እንዲኖራቸው ማድረግ ነበር፡፡[12] የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ጠበቃ ነን የሚሉት ህውሃት፤ ኦህዴድና መሰል ብሄርተኞች በሚያስተዳድሩት ክልል ፍፁም በሌለበት በአማራ ክልል ከሶስት በላይ ልዩ የብሄረሰብ አስተዳደሮች ተቋቁመዋል፡፡ ይህ በክልሉ የውጭ ጣልቃገብነትንና የውሥጥ መሳሳብን አሳድጓል፡፡

ለማጠቃለል ያክል በብሄርተኛው የአገዛዝ ዘመን አማራ ከመንግስት የፖለቲካ ስልጣን ተገልሏል፡፡ በኅብረ-ብሄራዊም ሆነ በብሄር አደረጃጀት  የተሰለፈው የአማራ ኃይል ልክ እንደ ንጉሱና የደርግ ዘመን በአገራዊ አጀንዳዎች በመያዙና በጠላትነት የፈረጁትን ቡድኖች ጠላት አድርጎ ለመታገል ባለመወሰኑ ምክንያት በአዲሱ የፌደራል መንግስት የአማራን ህዝብ  ጥቅም መብትና ደህንነት ማስጠበቅ ሳይችል ቀርቷል፡፡ ከብዙ በጥቂቱ ተገቢውን የፖለቲካ ውክልና ሳያገኝ በመቅረቱ ከመንግስታዊ ስልጣን ተገልሏል፤ ፍትሃዊ ባልሆነው የክልል አወቃቀር ሰፊ ግዛቶቹን አጥቷል፤ ኢፍትሃዊ ለሆነ የበጀት አመዳደብ ሰለባ ሆኗል፤ ባልመከረበትና ባላፀደቀው ህገ-መንግስት እንዲተዳደር ተገድዷል፡፡ ክልሉ የአማራ ማንነት በሌላቸውና አቅመ-ቢስ አማራዎች እየተመራ፤ በብሄርተኛው የአገዛዝ ዘመን በሙሉ የመዋቅራዊና ስርዓታዊ ጥቃት ሰለባ ሆኗል፡፡[13] አስገራሚው ነገር እነዚህ ሁሉ ችግሮች ተጋፍጠውበት እንኳ፤ አማራ ጠንካራ አደረጃጀት መፍጠርና በህልውና ስጋቶቹ ላይ መምከር አልቻለም፡፡ ህውሃት ከማዕከላዊ መንግስት እየተገፋ በነበረበት ወቅት የተመሰረተው የአማራ ብሄራዊ ንቅናቄ/አብን/ እኤአ በ2021 እስከተከናወነው አገራዊ ምርጫ ድረስ ህዝብን በማንቃት ጥሩ ተሳትፎ ያደረገ ቢሆንም ከምርጫ በኋላ ይህ ነው ተብሎ ሊገለፅ በማይችል ምክንያት ራሱን አዳክሞ አማራን ማታገል ተስኖታል፡፡ በጥቅሉ አብዛኛው አማራ የህልውና አደጋ የተጋረጠበት መሆኑን ቢረዳም፤ይህ ጥናት እስከተጠናቀቀበት እኤአ እስከ አፕሪል 2023 ድርስ ጠንካራ አደረጃጀት መፍጠርና ለጠላቶቹ ምላሺ መስጠት አልጀመረም፡፡

***መደምደሚያ***

[12] ዮቃለ ሠፈጀ ለቀባዮቾ፤ ለቶ ለዝሠፉው ነጋሺ፤ ለቶ ዉልዱ ለባተ፤ኮሎኔለ ለባተ ሠኮንን፤ ኮሎኔለ ባምሳኩ ለበበ፤ ለቶ ዮኔሰው ገፈሠው፤ለቶ ቃለ ምንተሰኖት፤ለቶ ጋኛው ተሰማ፡፡

[13] ዮኢትዮጵያ ፌደራላዊዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-ሠገ-ሠንግስትን ተሠልከት፡፡

የአንድ ታሪክ ሁነት መንስኤ ለዚያው ታሪካዊ ሁነት ዕውን መሆን አስተዋፅኦ ያለው ሌላ መንስኤ አስከትሎ የዚያ ታሪክ ክስተት መነሻ ምክንያት መሆኑን ያቆማል ወይም ይቀጥላል፡፡ ይህ ሂደት በታሪክ ጥናት ለውጥና ቀጣይነት (change and continuity) በመባል ይታወቃል፡፡ በብሄርተኞች የትግል ጉዞና አገዛዝ ዘመን የአማራ ህዝብ ጥቃት ፀረ-ፊውዳልና ፀረ-አማራ ትግሎች ከተጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ከተከሰቱ ዘርፈ ብዙ መንስኤዎች ይመነጫል፡፡ እነዚህም መንስኤዎች አንዱ ከአንዱ ይመዘዛሉ፡፡ መንስኤዎቹ በለውጥና ቀጣይነት ህግ መሰረት በአንድ ዘመነ መንግስት ታይተውና ሌላ የውድቀት መንስኤዎችን አስከትለው ጠፍተዋል ወይም በቀጣነት የችግር ምንጭ ሆነው ቀጥለዋል፡፡ ከብዙ በጥቂቱ ለመዳሰስ ያክል በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የአማራ ውድቀት መንስኤዎች ናቸው ተብለው ከሚታሰቡት የውስጥ ሺኩቻ፣ ነባራዊ ችግርን አለመገንዘብ/አለማንበብ፣ አለመደራጀት፣ የአማራ ብሄርተኝነት እንዲፈጠር እና እንዲያድግ አለመስራትና የመሳሰሉት ከንጉሱ ሥርዓት በኂላ አንዳንዶቹ ሌሎች የውድቀት መንስኤዎችን ተክተው ሲጠፍ አንዳንዶቹ ደግሞ በችግር ምንጭነታቸው ቀጥለዋል፡፡ ለምሳሌ ያክል የአማራው ጉልህ ድክመቶች የነበሩት ነባራዊ ችግርን አለማንበብ፣ ጠንካራ አደረጃጀትና የአማራ ብሄርተኝነት አለመፍጠር በደርግ አስተዳደር ቀርቶ በኢህአዴግ ዘመንም ቀጥለዋል፡፡

በመሆኑም በደርግ ዘመን የታዩ የአማራ ውድቀት መንስኤዎች ከንጉሱ ዘመን የተሻገሩና በዚያው ዘመን የተፈጠሩ ሁነው እናገኛቸዋለን፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ወቅታዊ ችግርን አለመረዳት እና አለመደራጀት ከንጉሱ ዘመን የተሸጋገሩ የአማራ ውድቀት መንስኤዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ያሮጌው ዘመን ችግሮች የአማራን ህዝብ ለዘርፈ ብዙ ጉዳት በማጋለጥ ለአሁኑ ውድቀቱ አዳዲስ ችግሮችን/መንስኤዎችን/ ወልደውለታል፡፡ ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያክል በቀይ ሺብርና ሌሎች ዘመቻዎች ምክንያት የተከሰተውን የትውልድ ክፍተት፣ ከሶሻሊስት ርዕዮት የመነጩ የኢኮኖሚ ድቀትና የባህል ስብራት፣ በደርግና ኢህአዴግ ጦርነት ምክንያት የተከሰቱ ሰብአዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከላይ የተጠቀሱት መንስኤዎች ውጤት ናቸው፡፡ እነዚህ የታሪክ ክስተቶች አዲስ የአማራ ህዝብ ችግሮች ወይም የውድቀቱ መንስኤዎች በመሆንና ሌሎች ችግሮችን በማስከተል የአማራን ጥቃት አፋጥነዋል፡፡ የቅድመ-አብዮትና የደርግ ዘመን የአማራ ችግሮች ድምር ወጤት የሆኑት ደግሞ አማራን ያገለሉ ብሄርተኛ ቡድኖች

መንግስታዊ ስልጣን መቆጣጠር፣ አማራ ያልተሳተፈበት ህገ-መንግስት መቀረፅና የአማራ ጥቃት መዋቅራዊና ስርዓታዊ መሆንና የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡ በጥቅሉ አማራ ከላይ የተጠቀሱት አንዱ ከአንዱ የሚመዘዙ ችግሮች ሳይጋረጡበት፤ በጠላትነት የፈረጁትን ቡድኖች የትግል ጉዞ ተገንዝቦ፤ ሲደራጁ መደራጀት፤ ሲያጠቁት ማጥቃት ሲገባው፤ ጠላቶቹንና ወዳጆቹን እንኳ መለየት ተስኖት፤ በብሄርተኞች የትግል ዘመን ከአጥፊዎቹ ጋር አጋርነት ሲመሰርት ታይቷል፡፡ ይህ ያልተጠና ጉዞ ብሄርተኛው ቡድን መንግስታዊ ስልጣን ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ የሰው ልጅ ባሳለፈው የታሪክ ዘመኑ ተፈፅመዋል ተብለው ለማይታሰቡ ሁለንተናዊ ጥቃትና ህዝባዊ ውድቀት አብቅቶታል፡፡ በሶስቱ የአገዛዝ ዘመናት የደረሰበት ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊ፤ ማህበራዊና ባህላዊ ድቀት የኋላ የኋላ የገጠመውን የህልውና ችግር ለመቀልበስ ሙሉ አቅሙን አሟጦ እንዳይጠቀምና ችግሩን በአጭር ጊዜ መቆጣጠር እንዳይችል አድርጎታል፡፡ከዚህ አዙሪት ይወጣ ዘንድ የአማራ ህዝብ ከላይ ከተጠቀሱት ታሪካዊ ስህተቶች ተምሮ ራሱን ከህልውና ስጋት ነፃ ማድረግ የቅድሚያ ቅድሚያ ስራው መሆኑን መረዳት ይገባዋል፡፡

## ዋቢ መፅሐፍት


Abadir M. Ibrahim. (2018). “Ethiopia’s Revolutionary Democracy as an AuthoritarianNeoliberal Discourse, *International Journal of Ethiopian Studies*, Vol. 12, No. 1, 17-50.

Abdul Mohamed. (2010). *The National Question*, eds. Bahru Zewde, in Documenting the EthiopianStudent Movement: an Exercise in Oral History, Ethiopia: Addis Ababa, Forum for Social Science.

Abbink Jon. (2011). Ethnic-based federalism and ethnicity in Ethiopia: reassessing the experiment after 20 years”, *Journal of Eastern African Studies* Vol. 5, No. 4, 596-618.

Asafa Jalata. (1995). The Emergence of Oromo Nationalism and Ethiopian Reaction”, *Social Justice*, Vol. 22, No. 3 (61), Racial & Political Justice,165-189.

Bahru Zewde. (2002). *A History of Modern Ethiopia, 1855-1991*, Second Edition, James Carry: Oxford. (2010). *Introduction*, eds. Bahru Zewde, in Documenting the Ethiopian student Movement: an Exercise in Oral History, Ethiopia: Addis Ababa , Forum for Social Science. (2014). *The Quest for*

*Socialist Utopia: The Ethiopian Student Movement c. 1960-1974*, AddisAbaba:

Addis Ababa University press. (2008b). The Challenge of the New Millennium: Renaissance or Reappraisal?, *International Journal of Ethiopian Studies*, 2008, Vol. 3, No. 2, 33-47. (2008a). *Society, State and History: Selected Essays*, Addis Ababa, Addis Ababa University Press.

Balsvik Randi Ronning.(1985). Haile Sellassie's Students: The Intellectual and Social Background to Revolution, 1952-1974, Addis Ababa: Addis Ababa University Press.

Beken Christophe Van der. (2015). "Federalism, Local Government and Minority Protection in Ethiopia:

Opportunitiesand Challenges", *Journal of African Law*, Vol. 59, No. 1, 150-177.

Bennett Jon. (1983). Tigray: Famine and National Resistance", *Review of African Political Economy*, No. 26, Sudan, 94-102.

Brietzke Paul H.(1995). "Ethiopia's "Leap in the Dark": Federalism and Self-Determination in the New Constitution", *Journal of African Law*, 1995, Vol. 39, No. 1, 19-38.

Chege Michael. (1979). "The Revolution Betrayed: Ethiopia, 1974-9",*The Journal of Modern AfricanStudies*, Vol. 17, No. 3, 359-380.

Clapham Christopher. (1987). Revolutionary Socialist Development in Ethiopia , *African Affairs*, Apr. 1987, Vol. 86, No. 343, 151-165.

Ezekiel Gebissa.,The Italian Invasion, the Ethiopian Empire and Oromo Nationalism: The Significance of the Western Oromo Confederation of 1936", *Northeast African Studies*, 2002, New Series,9, 3, (2002),75-96.

Eyayu Lulseged. (1994). Social, Economic and Political Discontent in Ethiopia as Reflected in Contemporary Amharic Songs, (Mid 1950s-Mid 1970s): *Journal of Ethiopian Studies* , Vol. 27,No. 2, 21-43.

Gebru Tareke.(2000). The Ethiopia-Somalia War of 1977 Revisited, *The International Journal of African Historical Studies,* 2000, Vol. 33, No. 3, 635-667.

González-Ruibal, Alfredo. (2010). Fascist colonialism: the Archaeology of Italian outposts inwestern Ethiopia (1936-1941), International Journal of

Historical Archaeology 14(4): 547-574.

Halliday Fred and Molyneux Maxine. (1982). Ethiopia's Revolution from Above, MERIP Reports, Jun., 1982, No. 106, Horn of Africa: The Coming Storm, 5-15.

Joireman Sandra Fullerton. (1997). “Opposition Politics and Ethnicity in Ethiopia: We Will All Go down Together”, *The Journal of Modern African Studies*, Vol. 35, No. 3, 387-407.

Keller Edmond J.(1985). “State, Party, and Revolution in Ethiopia”, *African Studies Review*, 28, 1, 1-17. (1995). “The Ethno genesis of the Oromo Nation and Its Implications for Politics in Ethiopia”, *The Journal of Modern African Studies*, Vol. 33, No. 4, 621-634.

Kidane Mengisteab. (2001). “Ethiopia's Ethnic-Based Federalism: 10 Years after”, *African Issues*, 2001, Vol. 29, No. 1/2, Ethnicity and Recent Democratic Experiments in Africa,20-25.

Legesse Lemma.(1979). “The Ethiopian Student Movement, 1960-1974: A Challenge to the Monarchy and Imperialism in Ethiopia”, *Northeast African Studies*, 1979, Vol. 1, No. 2, 31-46.

Levine Donald N. (2005-2006). “The Masculinity Ethic and the Spirit of Warriorhood inEthiopian andJapanese

Cultures”: *International Journal of Ethiopian Studies*, Vol. 2, No. 1/2 (Summer/Fall 2005-2006), 161-177 ( 1961). “Haile Selassie's Ethiopia: Myth or Reality?” *Africa Today*, May, 1961, Vol. 8, No. 5,11-14. (2012). “A Revised Analytical Approach to the Evolution of Ethiopian Civilization”, *International Journal of Ethiopian Studies* , Vol. 6, No. 1/2 (2012), 29-70.

Maimire Mennasemay. (2005-2006). “Ethiopian Political Theory, Democracy, and Surplus History *International Journal of Ethiopian Studies*, Vol. 2, No. 1/2, 1-32.

Markakis John. (1989). “Nationalities and the State in Ethiopia”, *Third World Quarterly*, Oct., 1989, Vol. 11, No. 4,118-130.

Ottaway Marina. (1977). “Land Reform in Ethiopia 1974-1977”, *African Studies Review*, Dec., 1977, Vol. 20, No. 3, Peasants in Africa, 79-90.

Paulos Milkias. (2003). "Ethiopia, the TPLF, and the Roots of the 2001 Political Tremor", *Northeast African Studies*, New Series, Vol. 10, No. 2, 13-66.

Tesfaye Aaron. (2005-2006). "Identity Politics, Citizenship, and Democratization inEthiopia", *International Journal of Ethiopian Studies*, , Vol. 2, No. 1/2, 55-75.

Teshome G. Wagaw (1980-81/1981). Emerging Issues of Ethiopian Nationalities: Cohesion or Disintegration, Northeast African Studies, Vol. 2/3, No. 3/1, 69-75.

Vaughan Sarah. (2003). Ethnicity and Power in Ethiopia, PhD Thesis, The University of Edinburgh.

Vestal Theodore M. (1999). *Ethiopia: A Post-cold war African State*, Westport: Praeger Publishers.

Yohannis Abate (1980-81/1981). "Ethiopia: The Origins of Military Intervention", *Northeast African Studies*, Vol., 2/3, No. 3/1 (1980-81/1981), 1-14.

Young John. (1996). The Tigray and Eritrean Peoples Liberation Fronts: A History of Tensions and Pragmatism, *The Journal of Modern African Studies*, Vol. 34, No. 1, 105-120.

ባህሩ ዘውዴ (2000).*የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983, ተሻሺሎ የታተም* አዲስ አበባ, አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ.(2011). የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ አሻራ ፤በብሄረሰብ ጥያቄ ላይ ፣ሀገረ ብሄርግንባታ በኢትዮጵያ ፤ ስውጥ በቀጣይነት ውስጥ፤ሲመገዚየም፣ ቢሸፍቱ.

ብሄረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (1993 ዓ.ም.) *ፅናት: በፋሽስታዊ ጭፍጨፋና አፈናያልተንበረከከው የኢትዮጵያ ህዝቦች* ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ የተጋድሎ ታሪክ, 1972-1982, አድስ አበባ: ሜጋ ህትመት ኢንተርፕራይዝ.

ሙሉቀን ተስፋው. (2008). *የጥፋት ዘመን: ከ1983 እስከ 2007 ዓ.ም በዐማራ ሕዝብ ላይየተፈፀመ ዘር ማፅዳት፤* አድስ አበባ.